
# የአራዳው ታደሰ



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከጳውሎስ ኞኞ

# የአራዳው ታደሰ

ከጳውሎስ ኞኞ

## ማውጫ

ምዕራፍ ፩ ........ 7
ምዕራፍ ፪........ 14
ምዕራፍ ፫ ........ 19
ምዕራፍ ፬ ........ 27
ምዕራፍ፭........ 29
ምዕራፍ ፮ ........ 37
ምዕራፍ ፯ ........ 46
ስለደራሲው በጥቂቱ ........ 51

ይህችን መጽሐፌን ለተወለድኩባት ለቁልቢ፤ ላደግሁባት ለድሬዳዋ፤ በጠቅላላው ለሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት መታሰቢያ አድርጌአታለሁ።

ከታተመችበት ወር አንሥቶ ላንድ ዓመት የመጽሐፌ የግሌ ነው ከአንድ ዓመት በኋላ መብቱ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ይሁን፤ ከወሰንኩት ጊዜ በኋላ አሳትሞ ለመሸጥ የፈለገ ሁሉ ከድርሰቴ ሳይቀንስም ሆነ ሳይጨምር ሊያራባው ይችላል።

ስሜን ሳይሰርዝ «አሳታሚው እገሌ» ብሎ ማንም ኢትዮጵያዊ ከፈለገ እንዲያራባት የደራሲነት መብቴን ለቅቄ አለሁ፤ አሳታሚው የግሉን የመግቢያ ሐተታ በስሙ ቢጽፍ እኔም ሆንኩ ወራሼ አንቃወምም።

የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች።

እንዲህ ሆነ፤ ይህችን መጽሐፌን በተወለድኩ በ፳፫ኛው ዕድሜዬ በ፲፱፻፺፬ ዓ.ም አዘጋጀኋት፤ ብዙ አልለፋሁባትም፤ አልተራቀቅሁባትም፤ ያን ኮፋሽ ማዕረግ «አዋቂ» እሰኝባታለሁ፤ ብዬ አልከጀልኩባትም፤ ደራሲዎችን ልወዳደርባት ከገበያ አላዋልኳትም፤ «የዘመኔ ሴቶች ትልክስክሶች ናቸው» ልልባት አላሰናዳኋትም፤ ደስ የሚያሰኙኝ «የሀገሬ ሴቶች እጅግ ጨዋዎች ናችወ» አላልኩባትም፤ ወንዱን ልነቅፍባት ብዬ አልተነሣሁም፤ ግና «ልብ የሌላቸው አሉ ለምን ከቄራ ሔደው ልብ አይገዙም» ልልባት ያሰብኩ መሰለኝ። ነው፤ ሳይሆንም አይቀር።

መጽሐፌን ያዘጋጀኋት ሚስት የሌለኝ የሚስት ደሀ ሆኜ ነው፤ በድብቁ ጨለማ በር በላዬ ተዘግቶ ጭር ባለበት ክፍሌ የአዲስ አበባ ውርጭ ተጨምሮበት የውሻ አፍንቻ ከሆነው መኝታዬ ላይ እንቅልፍ አልወስድ እያለኝ ግርመኛውን ሌሊት ስታገለው ይህችኒ ድርሰቴን አልጋዬ ላይ ተከዝኩባት።

በድርሰቴ ውስጥ የፈጠርኳቸው ሰዎች ልሙጭ ያሉት ባለጌዎች ናቸው፤ ብልግናቸውም እኔን ጨዋውን እንኳን አባለገኝ፤ ያየሁባቸውን ሁሉ አወራሁላችሁ፤ አፈጻጸሜ አይቅፈፋችሁ፤ ብልግና የምንላቸው ነገሮች በሀገራችን ስነ ጽሑፎች እጅግ ያልተለመዱ በመሆናቸው እኔም መቼም እንደእናንተው ጨዋ ነኝና ዓይናፋርነቱን እያበዛሁት «ተኝተው ያደሩበትን ሌንሶላ ገረዱ ብርቅነሽ አጠበች......እንደዜ ብቻ ዋይ ብላ ዝም አለች....... ከንፈሬ አበጠብኝ እኮ ብትለው የኔ ይበልጥልሻል አላት....... መሐረቤን ፍራሹ ሥር ረስቼው ስለ ነበር......ሩብ ሰዓት ተኝተው....... ደሜን እያዘራሁ» እነዚህን የመሳሰሉ ንግግሮች እየተሽኮረመምኩ አግብቻለሁና ስታነቡ አደራ እያፈራችሁ የባሰ እንዳታሳፍሩኝ።

ለኔ በሕይወቴ ለጋብቻ የጠፋብኝን ሴቶች ቆንጆዋንም፤ ፉንጋዋንም፤ ደሀዋንም፤ ሀብታሟንም ልጃገረዷንም፤ ፈቷንም ብልጧን፤ ቂሏንም፤

ሞያሌያሚንም፤ ይቺንም፤ ይቺንም ፈጥሬ ፈጥሬ በድርሰቴ ውስጥ ሞጀርኳቸው። የማዝነው የነዚህ ሁሉ ፈጣሪ ሆኜ የሚስት ደሀ በመሆኔ ነው፤ ብቻ ብልግናቸው እያናደደኝ ጠላኋቸው እንጂ ባጣ ባጣ ቂልና ሞያሌም አላጣም ነበር።

መጽሐፌን ስታነቡ የብዙ ሰዎችን ስም ታገኛላችሁ፤ በስሞቹም ማንንም ባለ ስም በሞክሼነታቸው ይቅርታ አልጠይቅም፤ አባት ለልጁ ደስ ያለውን ስም ይሰይማል። እኔውም በድርሰቴ ውስጥ ላሉ ሰዎች ደስ ያለኝን ስም ሰይሜላቸዋለሁ።

ፈጣሪዬ ሥላሴ ናቸው ለመጽሐፌ ፈጣሪዋ ደግሞ እኔ ነኝ፤ ሥላሴ ባፈጣጠራቸው ደህና ሀብታም፤ በሽተኛና ጤናማ ጨዋና ባለጌ እንዲሁም የለባቸውም፤ ያስፈለጋቸውን በማድረጋቸው ወቃሽና ከሳሽ የለባቸው፤ ወቃሽ ቢኖርም አይሰሙትም። መጽሐፌን ፈጠርኳት፤ እንዳፈጣጠሬም በመጽሐፌ ውስጥ ላሉ ሰዎች ፈላጭ ቆራጩ ባለሥልጣን እኔ አቶ ጳውሎስ ኞኞ በመሆኔ አንዱን ደሀ፤ ሌላውን ሀብታም፤ ይቺኛዋን እንዲህ፤ ያቺኛዋንም እንዲያ በማድረጌ የድርሰቴ ሰዎች አይከሱኝም አይወቅሱኝምም፤ ቢወቅሱኝም አልሰማቸው።

መጽሐፌ ፍጹም ልብ ወለድ ናት፤ ነገር ግን ያጻጻፌን ዓላማ ብዙ ጊዜ የምሰማውንና የማውቀውን እንዳጫጭር ታሪክ እያረኩ ጻፍኩት። አነሳሴም ላገባ በገበያ የምስማማቸውን ሚስቶች እንደ ታደሰ ዓይነቱ ጩልፋት እያደናቀፈ ስላስቸገረኝ ነዶኝ ነው፤ ቢሆንም ጽሑፌ ፋይዳ አይኖራትም።

ተተብትቦ መቻ በጠፋው ኑሮአችን እየተግተለተልን ትዳር ሳንይዝ ወንዶችም ሴቶችም ባንድ አረጀን፤ ፍቅር በወረቀት የሚለጠፍ ቴምብር ሆነ፤ መዋደድ በከንፈር አለቀ፤ ተሸማማች ሞልቶ ደላላዎች የትዳርን ገበያ በተኑት፤ ጩልፋቶቹ አላሻምት አሉ። ነዶኛል እንደ አነዳዴም የሥላሴን ፍጡር ገድዬ ከምገደል እራሴ እየፈጠርኩ መግደሉ ፋታ የሚሰጠኝ መሰለኝ።

<u>ባለትዳሮች፤</u> ጥሩ ሚስት ያገኛችሁ ወንዶች እግዚአብሔር አድሏችኋልና ተመስገን እያላችሁ ኑሩ፤ መልካሙን አባወራ ያገኛችሁ ሴቶችም ደላላዎችን ሳትሰሙ ለት ሰጥ ብላችሁ ኑሮ፤ መበሳጨቱን፤

መናደዱን፤ አልጋ መደብደቡን፤ ትራስ አቅፎ ማደሩን፤ ከገረዱ ጋር አብሲት መቆጣጠሩን እኛ የትዳር ምስኪኖች ወንዶች እንችልላችኋለንና የተጋባችሁ በፈጠራችሁ ይሁንባችሁ እንዳትፋቱና በውጭ እንዳትሞቱ።

ትዳር የሚያንገሸግሻቸው መኖራቸውን አውቃለሁ፤ በዚች አባባሌም እንደሚነቅፉኝና ያልሠለጠነው ጅላጅል እንደሚሉኝ እተነባለሁ፤ ግና ክብድ የለኝም፤ አፈጣጠራችን ለየቅል ነውና ነው።

# ምዕራፍ ፩

ጣይቱን አባቷ ብቻ አይከፋባትም፤ እናቷ ወይዝሮ ጣዲቄም ያው ናቸው፤ ደጋን አያያዝ እወቂ እያሉ አጉብጠዋታል፤ ንደፊ እያሉ ነድፈዋታል፤ አክርሪው በማለት አክረዋታል፤ ፍተይ እያሉ አፍተልትለዋታል፤ ዶሮ ሥሪ እያሉ ፍቀዋታል፤ ቡና አፍሊ በማለት አጥቁረዋታል፤ አብሲት ጣይ እያሉ አመድማዶ አድርገዋታል፤ በርበሬ ቀንጥሽ እያሉ ለብልበዋታል፤ እሳት እንድጂ እያሉ አንድደዋታል።

ከዚሁ ሁሉ ጣይቱን የሚያናድዳት የሚያበሳጫት ነፃ ሆነው ነፃነት እንዳላቸው ሴቶች ሁሉ ፉር ያለመለቀቋ ነው፤ ለሁል ጊዜም ባይሆን ያልፎ አልፎውን ትመኛለች፤ ግና የአቶ አጎናፍርና የወይዘሮ ጣዲቄ ልጅ ነች።

አንድ ቀለታ አቶ አጎናፍር ወደ ሥራቸው ወይዘሮ ጣዲቄ ደግሞ ገረዳቸውን በላይነሽን አስከትለው የታመሙ እኅታቸውን ወይዘሮ ትደነቂያለሽን ጥየቃ ሄዱ፤ ጣይቱ ግን ለምሳ የሚሆን ወጥ ትሠራ ነበረች፤ እጅና እግሯ ምድጃው አጠገብ ቢድበሰበሱም ጣይቱ ግን በዚያ እንጨትና የማድ ቤት ዕቃ ብቻ በታጎረበት ማድ ቤት ውስጥ አልነበረችም።

አንድ እጅግ አስጨናቂና አፈኛ የሆነ ኃይል ደቁሶ ይዟታል፤ ያም የሰረጸባት ኃይል አላስተነፈሳትም፤ ቆየትየት እያለች ያፈናትን ኃይል በኃይል ኡህ ትለዋለች፤ ሆኖም ጨርሶ አይወጣላትም፤ ጣይቱን ያስጨነቃት አንድ ኃይለኛ ኃይል አለ፤ ጣይቱ በምንም መንገድ በምንም ዘዴ በምንም ምክንያት በምንም ሁኔታ ያን ኃይለኛ ኃይል ልታስወግደው ወይንም ልትተነፍሰው ወይንም ደግሞ ልትተወው ወይንም ከኃይሉ የበለጠ ኃይል ልታገኝ አልቻለችም።

ጣይቱ ጉንጯን እየደፋች ዓይኗን እንዳፈጠጠች ሥራሥሮችዋን እንዳገታተረች ጡንቾቿን እንዳስቆጣች ከልቧ ትርግታ ጋር እየተናዘረች ከቧንቧው በጣሳ ውሃ ቀድታ ከማድ ቤት ገባ እንዳለች «የአየር ዝንባዝንቦች፤ በክንፍ በራሪዎች፤

አውሱኝ ነፃነት፤

አልሙት በባርነት» አለች፤ ቀጥላም ኃይሏን በኃይል ተነፈሰች፤ ግና አልወጣላትም፤ ወጡን እያማሰለች፤ «ጊደር ዕድለኛ ነች፤ በፈቃድዋ እናትዋን ተከተላለችና» ብላ ተከዘች።

ከጎረቤታቸው አሮጊቷ እመት ሙሉነሽ እንዴት አደራችሁ ቢሉ «ደህና» የሚል መልስ ብቻ አገኙ በሆዷም «አሮጊት ባልቴቶች ዕድሜያቸውን የፈጁ፤ ደግሞ ልጅ መልሰው የጃጁ» ስትል እመት ሙሉነሽ ከጣይቱ ዘንድ ገብተው እሜቴ ወዴት እንደ ሔዱ ጠይቀው ሲመጡ ሰላምታ እድትነግርላቸው ለጣይቱ ነግርወ ተሰናብተዋት ሔዱ፤ ጣይቱም ከዚያው ሥፍራዋ ተቀምጣ «በውኑ ታድለዋል አምላክ አፍቅሮአቸው፤

የኔው ዓይነት ኑሮ ሕጉን ገፎላቸው

ተቆጣጣሪ የለ ቢገቡ ቢወጡ

ማንም ምን ቢሆን በምንም አይለማመጡ

የሰው ልጅነቴ አፈነኝ በሲቃ

ተጨነቅሁኝ

ማሰንሁኝ

ለፋሁኝ

ይብቃ»

እንጨት ቆስቁሳ «እርግማን ምንድነው ትርጉሙስ እንዴት ነው? ረጋሚውስ ማነው? እናንተስ ብትሆን? ኧረ አባትስ ቢሆን? ምንድነው? ለምን ነው? ኧረ ለምን ነው ጭንቁ? በኔ ጊዜ፤ በኔ ዘመን፤ በኔ ወጣትነት፤ በኔ አፍላነት እናቴ የልጅነቷን ረሳች፤ በሱ ጊዜ በሱ ዘመን፤ በሱ አፍላነት፤

አባቴ አልፎት የመጣውን ልጅነት ዘነጋው፤ ለምን? በምን? ስለምን? መሆን አይገባውም» አለችኝ፤ ከዚያም ለጥቂት ጊዜ ከንፈሯን አለንቡጫ ቆየች።

ድስቱን አውጥታ ካስቀመጠች በኋላ «አባቴ ለናቴ የዚያን ጊዜ እንዲያ፤ በንዲያ፤ ስለንዲያ ለንዲያ እወድሽ ነበር ይላታል። እናቴም አባቴን በልጅነቴ የእንዲህ ጊዜ፤ በእንዲህ ስለንዲህ፤ ለእንዲህ እወድ ነበር ትለዋለች። እኔስ? የ - በ - ለ - ስለ ለምን ይነፈጉኛል? በምን ምክንያት? አልቻልኩም አቃተኝ ተሸነፍኩ ደከመኝ፤

በምን የተነሣ ለምን ነው የሚያመኝ?

ሰዎች ከሰው ጋር እንኑርስ ቢሉ

ለእኔ እንደሚሉት ለእንቶኔም ይበሉ። ያለዚያስ ሰው ከሰው ጋር ተዋዶ የሚኖርበት ምንድነው ምክንያቱ? መከባበሩስ ለምን ነው? በምን ይሆናል? በምን የተነሣ? በምን ምክንያት? በምን ሰበብ? አይገባኝም።

ሰው ለሰው መውደዱ ለምንድን ነው? ሰው ለሰው መሸቆጥቆቱስ የምን ዘዬ ነው? አባቴ ማነው? እናቲስ ደሞ ማናት? ልጃቸው ነኝ፤ አሞኛል፤ የባሰውን በሽታ ሆነብኝ ከብዶኛል፤ እነሱ ተጨማሪ ሸክም ሆኑብኝ፤ ልቤ ጠፍቷል፤ የለም የለም፤ ወላጆቼም ሊያገኙልኝ አልቻሉም! አቀቃታቸው!! ሰነፉ! የአባቴ አባት መሪጌታ ደሳለኝ ልጅ አላስወለዱም የእናቴ እናት እምዬ ሙላቷም ጭንጋፍ ወልደዋል፤ የሰው ልጅ ሰው ሆኖ ሰውን ካልወለደ

አንዱ በማያውቀው ባዱ ከፈረደ፤ ኑሮ እንዴት ሊሆን ይችላል? አይሆንም፤ ወደድኩት፤ አፈቀርኩት፤ አሻፈረንኝ፤ እምብዮ ከሁሉ አስበልጪ ወደዋለሁ፤ ወደድኩት! ወዶኛል፤ አፍቅሮኛል፤ ታዲያስ? የነሱ መጨቆን ምን ይባላል? ትርጉሙስ ለማን ይገብዋል? ይገባናል የሚሉ ቢኖሩ እታዘባቸዋለሁ።

«ለእግዚአብሔር ሁለት ልመና አቀርብለታለሁ፤ ከሁለቱ አንዱን እንዲፈጸምልኝም እማጸንበታለሁ፤ ይግደለኝ፤ አለዚያም ባፈር በገለባም ብሎ ከታደሰ ጋር ያገናኘኝ፤ ወዴንና ውዱንም ያዋጣልን፤ የማይሆን ከሆነ

ሞት! መሞት! ሞት ይምጣ፤ ይገባኛል መሞት፤ በእርግጥም ያስፈልገኛል» አለች።

ከቤት ብትወጣ ከአጥር ውጪ ታደሰን አየችው፤ ደንገጠች፤ ፈራች፤ ብርክ ያዛት፤ እንደ መሽኮርመምም አለች።

የታደሰ ጥርሶች ያማምራሉ፤ ጉንጮቹ በምላጭ አልተፈተጉም፤ ሲያያት ሳቅ በማለት ለሳቅ ንግግሩ ስቃ አነጋገረችው፤ ወዳጥሩ ተጠጋች፤ በዚያም ከታደሰ ጋር እጅግ አወሩ፤ ብዙም ተጫወቱ፤ ወዲያውም በአጥሩ ሾልካ ከታደሰ ጋር ሔደች፤ ጠፋች፤ አቶ አጎናፍርና ወይዘሮ ጣዲቄ ማንን ያናድዱ ይሆን?

//=//

ታደሰ ጣይቱን አገኛት፤ ደግሞም አገኛት ጣይቱም ታደሰን አገኘችው፤ ደግማም አገኘችው፤ «ሰዎች ሰው የሚሆኑት ከሰው ጋር በተገናኙ ጊዜ ነው» አለች፤ ማለቷንም ቀጥላ «ይህ ቀን ይህ ሰዓት ይህ ጊዜ በጠቅላላው ይህ ሁኔታ እንደወይት ይገኛል እያልኩ ናፍቄው ነበር፤ አገኘሁት፤ ያ - የሐሳብ የረዘመብኝ ጊዜ አሁን ሆነ፤ ይሆን ተፍቶ ሆነ ተተካ፤ ይደንቀኛል» አለች «ደግሞም» ብላ ወሬዋን ስትቀጥል ታደሰ አቋረጣት።

«ሰላቢ ነሽ በዓይንሽ ስለበሽኛልና» አላት፤ ወዲያውም ደግሞ እየተንጎራደደ ጥቂት ካሰላሰለ በኋላ እጁን እያሻሸ «የሴት ልጆች ውበት የወንዶች ማሠሪያ

«እህሁ ወዲያ፤ ወዲያ፤» አለና ወደ መስኮቱ ጠጋ ብሎ ውጪውን እያየ ተከዘ፤ ወዲያውኑም ዞሮ ፈገግ ብሎ «አሁንም ይደንቀኛል፤ ደግሞም ይገርመኛል፤ አሁንም እንደ ገና ይደንቀኛል፤ መልሶም ይደንቀልኛል» ብሏት ፊቱን ዞሮ በመስኮት ወደ ውጪ ያተኩር ጀመር።

ጣይቱ በምቹው ወንበር ላይ እንደ ተቀመጠች የታደሰን ጀርባ እያየች «ፍቅር አስጨነቀህ፤ አስጠበበህ፤ አምላክ ፈርዶብህ በውዴ ማቀቅህ፤ ታዱ? ታድዬ? በምን ሁኔታ ባስደስትህ ትደሰታለህ? ታዱዬ ንገረኝ እኮ? አውጋኝ» አለችው።

ታደሰ ውጪ ውጪውን እያየ በስተጀርባው «ያም ይሆናል፤ ደግሞም አዎን፤ ምን ልበል? በወኑ ውድሽ ያስጨነቀኝ ይመስልሻል? ፍቅር ቶሎ ግሎ ሲሆነው ገልጃጃ፤ ትርጉሙ ምንድነው? እንጃ እንጃ» አላት፤ ጣይቱ የመገረም መልክ ታየባትና «ያሁነኛው ንግግርህ ያስገርመኛል» ካሉት በኋላ መልሳ ደግሞ «እንጃ እንጃ፤ ያልከው ለምንድነው ታዱ?

ውቃቢህ ምን ይሻል፤ ምንድን ነው ልማዱ? ደግሞሳ ታደሰዬ? ባለፈው ጊዜ መገናኛ አጥተን» ብላ ሳጨርስ ታደሰ አቋርጧት ወደ ኋላው ይናገር ጀመር። «ያንን ተይው፤ አልፏልና - ያልነበርሺውን አሁን ከውጪ እንደማያው፤ አልፏልና፤ ያልነበርሺውን አሁን ከውጪ እንደማያት እንደዚያች ቢራቢሮ አደረኩሽ፤ ግና ምን ልበልሽ? ኧረ ምን - ምን - ልበልሽ? » አላት።

ጣይቱ ጥቂት ሴኮንዶች አመንትታ «ምን ትለኝ? » አለችው «አንድ ኃይል አፍኖኃል፤ አይደለም? ነው በለኝ፤ ከራስህ የሚበልጥህ ማንም ሆነ ምንም የለም፤ ጠላኸኝን? » አለችው።

ታደሰ ወደ ውጪው እያየ ሳቅ አለና በቀኝ እጁ የመስኮቱን መጋረጃ እየነቃቀሰ «በውነቱ ሰቶች ነቢይነትም አላቸው እወድሽ እንደ ነበረ እናውቃለን፤ እንደማውቅሽ ቆንጆ ነሽ፤ እንደምናውቀውም ውብ ነኝ። ታዲያ ብንጋባ የምንኳኋን ይመስልሻልን? » አላት።

ጣይቱ ባለችበት ምቹ ወንበር ላይ እግሮቿን አነባብራ በግራ ጉንዋ ጋደም ብላ በመደገፊያው ላይ እጅዋን አድርጋ በግራ እጅዋ ግራ ጆሮ ግንዷን ደገፍ ካደረገች በኋላ ላላት ማለቷን ቀጠለች «በእርግጥ ልጆች ያቦኩት ለራት አይበቃም የሚባለው እርግጥ ነው፤ ደግሞም እርግጥ ነው፤ ፍጹምም እውነት ነው፤ የጥምቀት ለታ ጃንሜዳ ተገናኝተን ከረሜላ ገዝተህልኝ ለብቻችን ተቀምጠን የፈረስ ላይ ገና የሚጫወቱት ስናይ ያልከኝን ዘነጋኸው? ያ - አረንቻታ የገዛኸው ልጅ ዛሬ አይገኝም እንጂ በመስከረ ነበረ» አሻቅባ «ሃሌ ሉያ የነበርክ አምላክ ሆይ!!» አለችና እንደገና የታደሰን ጀርባ እያየች «ያልከኝን ታውቀዋለህ፤ አውቀዋለሁም፤ ምናልባት ረስተኸው፤ ይሆናል፤ በርግጥም ረስተኸዋል፤ አዎን

ዘንግተኸዋል ደግሞስ የቃና ዘገሊላ ለታ የካ ከእናቴ ጋር አግኝተኸኝ ከእናቴ እንድነጠል አስደረገህ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ጀባ ባለው ጫካ ውስጥ ስናወጋ ምን አልከኝ? ኧረ ምን ነበር የተናገርከኝ? ረሳኸው? » ራስዋን ቀና አድርጋ «ኤሎሄ የሰው ልጆችን ልቦና የፈጠርክ አልፋ ኦሜጋ ሆይ መንበርህ ወዴት ነው? » አለች።

ጋደም ካለችበት ተቀምጣ «የሰው ነህ አልኩህ አይደለም አልከኝ፤ ወደድኩህ አልኩህ፤ ጠላሁሽ አልከኝ፤ ክብሬን፤ ክብሬን ማዕረጌን መከበሪያዬን መወዳጃዬን ገፈፍህ፤ ቅድስት የምባልበትን አረከስህ፤ እንደገናም ደግሞ» ብላ ሳትጨርስ ታደሰ እጆቹን ወደ ኋላ ደራርቦ ወደ መዝጊያው ዘንድ እየተራመደ ላለችው ሲል ጀመረ።

የቂሎች መሞኛ የሞኞቹ ወሬ

ክብሬ ክብሬ፤ ክብሬ፤ ክብሬ፤ የሚባልበት ፍቼ አይገኝም» ተመልሶ ወደ መስኮቱ እየተራመደ «ምናልባት ይገባኛል ትይ ይሆናል፤ ባለመግባታችንም አይከፋኝም፤ ነሽ ነኝና፤ ሆነ በሁለት መንገድ ነፃ አወጣሁሽ፤ አሁን ግን ክብሬ አልሽ፤ የኔሳ? ኧረ የዚያን ጊዜሳ? የካን ካመጣሽው ዘንዳ አንቺስ ከጫካው ምን አልሺኝ? ተናገሪ የአንዱን ጉድ የሚያወራ የራሱን ሰውሮ ነው፤ መታደስን እንድንሻ አባቴ አቶ ወልደ ማርያም ታደሰ አሉኝ፤ ጣይቱ ነሽና በጸሐይነትሽ ለሁሉ ብታበሪ ምን አለበት? »

ወደ መዝጊያው እየተመለሰ «የሚደንቅሽ ብዙ እንዳለ አውቃለሁ፤ እንዳለኝም እወቂ፤ ስላልኩ ተባልኩ በይ፤ ተባልኩን ብቻ አታዘውትሪ ወደድኩሽ፤ መልሼም ደግሞ ጠላሁሽ፤ እንዳልሽውም፤ ልበል» ልጆቹና ፊቱን ወደ ሰማይ አሻቅቦ «አቤቱ የሴቶችን ልብ የፈጠርክ ሆይ ምን ቻይ ነህ? » አለ።

ጣይቱ ስትመለስ «ፈጣሪ የሁሉንም ሁሉ ይስማ፤ እናት አባቴን ከዳኋቸው፤ ካንተ ዘንድ እመጣሁ እዛሬው ስምንተኛው ቀን ደስ አልተያየንም፤ ያለሁበትንም አያውቅም» አይኗን አሻቅባ ባለአክናፍ አማልክቶች ሆይ፤ ስለኔው ምን መከራችሁ? ምንስ ተባባላችሁ? ባለ

ጥቁሮቹ ጭራ መላእክቶች ሆይ ምንኛውን ብቅል ጠነሰሳችሁብኝ» አለችና ተከዝ ብላ «ስማኝ ታደሰ፤ ወዴት ልሒድ? ቦታውን ምራኝ፤ የምገባበትንም ቀዳዳ አሳየኝ» ብላ አዝና አቀረቀረች።

«ላልሸው ልበል» አላት ታደሰ «ሁሉንም ተይው፤ እርሺው፤ አታስታውሺውም፤ ደግሞም አታልቅሺ፤ ማንባትሽ ልነግርሽ» ብሎ አንዱን እግሩን ከምቹው ወንበር ላይ አድርጓል ጉልበቱን በክንዶቹ ተመርኩዞ ጎበጥ አለና «ያሰብኩትን ነገር ሁሉ አስጠፋኝ፤ አይዞሽ አትባቢ፤ የሴት ልጆች እንባ ቅርብ ነው ላይ ናቸው፤

በቶሎ ለማልቀስ ተሰጥዎ አላቸው፤ ከዚያም ሌላ ደግሞ ሴቶች ልጆች» እግሩን አውርዶ ወደ መስኮቱ እየሔዱ «በመባባታቸው የወንዶችን ልብ ለመስበር እንደሚችሉ አውቃለሁ፤ እርግጥ እንው» የመስኮቱን መጋረጃ በግራ እጁ ገልጦ ይዞ ወደ ውጪ እያየ «ሆኖም ደግሞ በእርግጥ ለመባባታቸው ምንም ዓይነት አስረጅ አይገኝላቸውም»

«በድንገት ወደ ጣይቱ መለስ ብሎ «አሁን መቶ ብር እሰጥሻለሁ፤ ሦስት ወር ድረስም ከሰላሳ ብር ያልበለጠ የቤት ኪራይ እከፍልልሻለሁ፤ ይህም በውነቱ ላንቺ ብቻ ያደረግሁት ከፍተኛ ዕርዳታ ነው» ፊቱን ወደ መስኮት ዞሮ ውጪ ውጪውን እያየ «ይህንንም ያናገሩኝ መናፍስት አስደነቁኝ፤ ለሴት ልጆች ኑሮ ሰፊ ነው አዲሳባ፤

ለምን ነው ጣይቱ ሆድሽ የሚባባ፤ በውነቱ በፍጹም ሊባባብሽ አይገባም፤ ታዲያ ባልኩሽ ትስማሚያለሽ? የማትስማሚ ቢሆን ብዙም መንገድ ነፃ ያወጣሁሽ ነኝና ደግመሽ ደግሞ በነፃ ልትሔጂ ትችያለሽ፤ ያለዚያም ደግሞ ጓድ እንደምትሆኝያቸው ዓይነት ይታሰብልኝ የምትይም ቢሆን ዛሬ ሰባት ቀንሽ ነው፤ በከፍተኛ ሒሳብ በሰላሳ አምስት ብር ልንለያይ እንችላለን፤ እወቂ የደንበኝነት ሂሳብ አልተቀነሰለትም» ብሎ ፈገግ አለና የኋሊት ሰርቆ አያት።

ለዚህ መልስ ጣይቱ እንደ ተከዘች «ይሁና» አለች። ጣይቱ ታደሰ የሰጣትን ገንዘብ ይዛ ከቤቱ ወጣችለት፤ ታደሰት ሁለቴ ተገላገላ፤ ፍቅሯ ያስጨነቀውን አግኝቶ ያን ጭንቁን ተገላገለ ወዶ የጣላት ጣይቱ ከቤቱ

ስለሔደችለት እንደገና ተገላገለ፤ ታደሰ አረፈ፤ ጣይቱ ከርታታ ልትሆን ሔደች።

# ምዕራፍ ፫

ፊታውራሪ ደባልቀው ሀብታም ናቸው፤ ሚስታቸው ወይዘሮ እጅጋየሁ የደጃች ከበደ ልጅ ቢሆኑም ፊታውራሪ ደባልቀውም በዘራቸው እንደ ብርሌ የጠሩ ጨዋ የጨዋ ልጅ ናቸው፤ በዚህ ምክንያት እልፍነሽ የታላላቅ ሰዎች ልጅና የልጅ ልጅ በመሆኗ ተከብራና ተፈርታ ትኖራለች፤ ፊታውራሪ ደባልቀው ከእልፍነሽ ሌላ ልጅ አልወለዱም፤ ብቻ አንድ ጊዜ በልጅነታቸው ከባላምባራስ ጉለቻ አርግዘው የ፯ ወር ጽንስ ተጠናውቷቸዋል።

እልፍነሽ የጌታ ልጅ በመሆኗ ያሻትን ታገኛለች፤ ይሔም ያንቀባርራታ፤ እልፍነሽ ለወላጆችዋ እሷው ብቻ በመሆንዋ ፊታውራሪ ደባልቀው ትከሳብኛለች እያሉ ተቆጥተዋትም አያውቁ፤ ወይዘሮ እጅጋየሁም ከተወለደች ጀምሮ አልቆነጠጧትም።

ወይዘሮ እጅጋየውሁ ልጃችን ቶሎ ባል ታግባ እያሉ ቢተውትም ፊታውራሪ ደባልቀው ግን እኩያዬን እፈልጋለሁ በማለትን አቆይተዋታል፤ እልፍነሽ እያደገች አይልኩም፤ የትልልቅ ሰዎች ልጆችም እየናቁ ላግባ ባይ ታጣ፤ እልፍነሽ ግን እያደገች ታሳጣ ጀመር።

እልፍነሽ ፳፫ኛዋን ስትይዝ መማርዋን ትታ ሥራ ለመያዝ ፈለገች፤ ስለዚህ ምክንያት ቤት መማር እንዳለባት አወቀች፤ አውቃም ገባች፤ እየተመላለሰችም፤ ታይፕና ሾርት ሐንድ ታጠና ጀመረች፤ የእልፍነሽ ዕድሜ የተማረ የተማረችበትን ጊዜ ያብዛባት እንጂ እልፍነሽ ለትምህርት ግድ የሌላት በወላጆችዋ ሀብት ተመኪ ነበረች፤ ጓደኞቿም «ብላክ ስቶን» እያሉ በደደብነቷ ያሚት ነበር። እልፍነሽ የወር አውቶብስ ቲኬት አስቆርጣ ከንግድ ትምህርት ቤት እስከ ጉለሌ እየተመላለሰች ትማር ጀመር። አንድ ቀን ለታ እልፍነሽ በ፫ ቁጥር አውቶብስ ሽቅብ ስትሄድ በዚያ ግፊያ መሐል አንድ መልከ መልካም ዛላውና አለባበሱ የሚያምር ወጣት እንደተገፋ አስመስሎ በእልፍነሽ እጅ ውስጥ አንድ ፖስታ አስጨበጠ እልፍነሽም ዞር ብላ ብታየው ሳቅ አለላት፤ ለጊዜው እልፍነሽ ለመናገር የአውቶብሱ ውስጥ

ሰው ብዛት አሳፍሯት ዝም ብትልም በቁታ አስተያየት ያን ወጣት ገርምማው ፈቷን አዞረች።

እልፍነሽ በቁጣ ፊቷን ብትመልስም ወጣቱ የሰጣትን ወረቀት አልመለሰችለትም፤ ምናልባት ወረቀቱን ስትመልስ ሰው ያየኛል በማለት ፈርታ ይሆናል። ወይንም ደግሞ በዚያ ሁሉ ሳተና መሐል በሷ ምክንያት ጠብና ሳቅ እንዳይፈጠር ይሉኝታ ይዟት ይሆናል።

አውቶብሱ ጊዮርጊስ ሲደርስ እልፍነሽ ወረደች፤ ወጣቱ ግን በአውቶብሱ እንደሆእን ተመለሰ፤ እልፍነሽ ፩ ቁጥር አውቶብስን ልትጠብቅ ሔደች፤ የወጣቱንም ወረቀት ከቦርሳዋ ከተተች።

እልፍነሽ ከቤትዋ ገብታ ወጣቱ የስጣትን ወረቅት ከነበበች ወረቀቱም አልፎ አልፎ «......መውደድ አዲስ ነገር አይደለም፤ የኔው ግን በሰው ላይ ያልደረሰ ፍቅር አብሮኝ ሸከሙ አጎበጠኝ........ፍቅሬ ሳልሞት.......ፍቅሬ......አድኚኝ......ብሞት ሥጋሽ በሕየትሽ በጸጸት ይጋያል.........ፍቅርዬ ያቺ አንቺን የያሁባት ቀን ጨልማ ቢሆንስ ኖሮ ያሁን ሥቃይ ባልደረሰብኝ ነበር.......ውድዬ........ልሞት ነውና አትግደይኝ........እንደ ክርስቶስ ሙት ማስነሳትንሽ ስለምተማመን ሙትሽ ነኝና ከግንዛቴ ፍቺኝ........አትጨክኚ.......መልሱን እጠብቃለሁ......ለመልካም መልስሽ ባለ ተስፋ ነኝ።

በፍቅርሽ የጋየው ታደሰ ወልደ ማርያም» በማግሥት እልፍነሽ በ፫ ቁጥር አውቶብስ ሰንጋ ተራ ላይ ስትሳፈር ታደሰ ጠብቋት ተከታሏት ተሣፈረ። እንዳጋጣሚ አውቶብሱ በሰው አልተመላም፤ መቀመጫ ሞልቷል፤ ታደሰም እንደ ገባ ደስ አለው፤ ከእልፍነሽ አጠገብ ተቀመጠ፤ በስተቀኙ እያያትም ፈገግ ሣቅ አለ።

እልፍነሽ በፈገግታው ፈገግ ብላ ቀኝዋ በመስኮት ውጪውን አየች፤ ታደሰ ተመቻችቶ ተቀመጠና ፈገግ አለ፤ አውቆብሱ ሽቅበቱን ሊያያዘው እስቲጀምር ድረስ በሙተያየትና በመሽኮርመም ዘገዩ።

እደገቱ ጉዞ ላይ ታደሰ ወደ ቀኙ ዞር ብሎ «መልሳችንሳ» የሚል ቃል ጣል አደረገ፤ እልፍነሽ ግን «ሆሆይ» ብላ ፊቷን ወደ ቀኝዋ ዞራ ዝም አለች፤

ታደሰ «በውኑ ለሞተ ሰው አይታዘንለትም» ቢል «የምሔድው ከል ልገዛ ነው» የሚል መልስ ከእልፍነሽ አገኘ።

ነገሩ አያስቅም ታደሰ ግን የቸከ አሳሳቅ ሳቀ፤ ቆየት ብሎም ወደ ቀኙ ዞር አለና «አውሪኝ» አለ፤ እልፍነሽ ፈገግ ብላ ዝም አለችው፤ ጥቂት ቆይቶ «ኧረ ሞቻለሁ አነጋግሪኝ» አለ፤ የዚህን ጊዜ እልፍነሽ «ሕያውና ሙታን እንዴት ሊያወራ ይችላል» አለችው።

ይህን የመሰለ አያወሩ ተጉዘው አውቶብሱ የዳግማዊ ምኒልክን ሲዞር እልፍነሽ በታደሰ እጅ ላይ ፖስታ ጣል አደረገችለትና ሲቆም ወረደች ታደሰም ተከትሏት ወረደ፤ አብሯት ሊሔድ ሲፈልግ «ክብሬን የምጠብቅ ክብር ያለኝ ልጅ ነኛን ተመለስ» ብትለው ታደሰ ክው ብሎ ተመለሰ፤ ከረቦ ከሚመታው ልቡ ጋር እየተርበተበተ ቁልቁል ወረደ።

ከልዑል ራስ መኮንን ቡና ቤት ገብቶ አንድ ሲናልኮ አዞ ተቀመጠ፤ ማንበብም ጀመረ «......ከመቃብር አልገባሁም እንጂ ሞትህ ገሎኛል - ውበቴ እንዳስደነገጠህ ሁሉ ሽቅርቃሮትህና ውብትህ አስደንግጦኛል፤ - ስታየኝ እንደ ቆየህ እጅግ ቀናት እኔም አይቼሃለሁ - አንተ በኔ ሞተሃል እኔ ደግሞ በአንተ ሞቻለሁ - የምታድነን ብትሆን አድንሃለሁ፤ - ውድዬ ያደረብህንና ያደረብኝን ጭንቀት በምን እንወጣዋለን? - እንደፈቀድከኝ ፈቅጄሃለሁና ማንኛውንም ነገር በጋብቻ እንፈጽመው - በሌላ በኩል ግን አልስማማም፤ - አየህ ታደስዬ ብዙዎች ላግባሽ ብለውኛል፤ እኔ ግን እንደ አንተ አልወደድኳቸውምና አልፈቀድኩም - አንተን እወድሃለሁ - ሽታዬ እንዴት ልሁንልህ - ታዱዬ ምን ትመከረኛለህ? - የምትፈቅድስ ቢሆን ካንድ ስውር ቦታ ተገናኝተን ቃል በቃል እናውጋ - መልስህን ጠባቂ ነኝ።

የፍቅርህ እሥረኛ እልፍነሽ ደባልቀው። ታደሰ ደስ ብሎት ወደ ቤቱ ሔደ፤ ለሊቱን መልሱን ጽፎ በነጋታው አውቶብሱ ላይ ሰጣት፤ በደብዳቤው ላይ «.......እቤት ወስጄሽ እንነጋገር - » ብሎ ከሌላ ዘንድ እንሒድ - » የሚል መልስ በሁለተኛው ደብዳቤ ላይ አገኘ።

ሐሙስ ለታ አውቶብስ ላይ ተገናኝተው በሚቀጥለው እሑድ ወደ ሾላ ሔደው ለመነጋገር ተስማሙ፤ እሑድ ደረሰ፤ ተገናኝተውም በ፺ ቁጥር አውቶብስ ወደ ሾላ ሔዱ በዚያም ስለ ጋብቻቸው ስለ ወደ ፊት ሰፊ ኑሮአቸው ሰፊ ንግግር ሲለዋወጡ ዋሉ።

በ፲፩ ሰዓት ገደማ በአውቶብስ ወደ ከተማ ተመለሱ፤ ሾላ ነበሩበት ጊዜ እልፍነሽ የታደሰን ቤት ዓይታ ስለ ኑሮው አያያዝ እንድትገምት ተስማምተው ነበርና ከሾላ መልስ ሠራተኛ ሠፈር ካለው ከታደሰ ቤት በቀጥታ ሔዱ።

ታደሰ ዘመናዊ ወጣት ስለሆነ የቤቱ አያያዝ ያስደስት ነበር፤ በዚህም ምክንያት እልፍነሽ ራሱን የቻለና ለኑሮው ታታሪ ወጣት በማግኘቷ ደስ አላት፤ ሲላፉና ሲያወሩም መሸ፤ በልመናም በማስገደድም አሳደራት፤ በማግሥቱም ከሥራ ሳይሔድ አብሯት ከቤት ዋለ፤ ተኝተው ያደሩበትንም አንሶላ ገረዱ ብርቅነሽ አጠበች።

በመጨረሻው ታደሰ ባደረገው ጥፋት ለፊታውራሪ ደባልቀው አማላጅ ሊልክና ከእርቅ በኋላ ሊጋቡ ተስማ፤ ስምንት ቀናት ያህልም ታደሰ ጨዋ ሰው በመፈለግ ላይ ነኝ እያለ አማላጅ ሳይልክ እልፍነሽን ከቤቱ አከረማት።

እልፍነሽ ታደሰ ቤት ከመጣች አሥራ አምስት ቀን ሆናት፤ ታደሰ የእልፍነሽን መጠለፍና በቅርብ ቀንም አማላጅ እንደሚልክ በደብዳቤ ጽፎ በፖስታ ቤት ለፊታውራሪ ደባልቀው ልኮ ነበርና የእልፍነሽ ወላጆችም «ምን ዓይነት ሰው ይሆን? » ከማለትና አማላጆቹን ከመጠበቅ በስተቀር በመከረሟ አልተጨነቁም ነበር።

//=//

እልፍነሽ ታደሰ ቤት በገባች በ፫ኛው እሑድ ቁርስ በልተው ጨዋታ ጀመሩ፤ ብዙ ከተጫወቱም በኋላ፤ «ምነው የአማላጆቹን ጉዳይ ቸል አልከው» ብትለው ታደሰ ቀና ብሎ ዓይቷት ፈገግ አለና «ምን አስቸኮለሽ? ማግባት ማለት ምን በቃ አለው» አላት።

ዓይን ዓይኑንን ታየው የነበረችው እልፍነሽ አንገቷን ቀለስ አድርጋ «አንተ ትቀልዳለህ መሰለኝ፤ እኔ ለራሴ ጨንቆኛል» አለች፤ ታደሰ አንድ መጽሔት አንስቶ ብድግ አለና መጽሔቱን እያገላበጠ እያየና የሚወዱ ነፃ ውጪያቸውን ይጋፋሉ፤ አንቺም እንደነኚያ መሰልሺኝ፤ ወላጆችሽ በባርነት ጨቁነው እንደያዙሽ አትርሺ፤ ነፃ ማውጣቴንም» ብሎ ሳይጨርስ

እልፍነሽ ጣልቃ ገብታ «ምም ልትል ነው? ደነገጥሁ አያያዝህ ያስደነግጣል፤ አባባልህም ያስደነብራል» አለች።

«እንደ እንግዳይቱ በቅሎ ቅድመሽ ደነበርሽ» አላትና ታደሰ ዞር ብሎ አተኩሮ እያያት «ለነኛ ለጨቋኝ ወላጆችሽ ምን አማላጅ መላክ ያስፈልጋል? አንቺ በገባ ምን የምጠቀም ይመስልሻል? ብታገቢኝስ ምን ፋይዳ አለሽ? አንቺን፤ ይቺን ያቺን የመሳሰሉት ሁሉ፤

ጋብቻ ጋብቻ ለምን ነው የሚሉ። አይዞሽ አትተከዥ፤ ከፋሽን? » ብሎ ወደ ግራው ዞሮ ፈገግ ብሎ ገረመማት።

«እግዚአብሔር ይፍረድብህ» ብላ እልፍነሽ እያለቀሰች ተናገረች «አናንተ ወንዶች እናንተ ጊዜ የረዳችሁ፤ በተላይም አንተ፤ ምን ተባብለን ምን ትለኛለህ? በውኑ ያ - ቃልህ በዚይ ይለወጣልን? ወንድ ነህ አልኩህ፤ እንደ መንደረተኞቹ ሴቶች ወሽከተህ ታዱ እህል ነበር፤ ዛሬ ግን ታደሰ ልበልህ፤ እንዴ» ብላ ሳትጨርስ አቋረጣት።

ይንጎራደድ የነበረው ታደሰ ወንበር ስቦ ከተቀመጠ በኋላ «ይብቃሽ ፌንጣ ብትቆጣ እግሯን ታስቆርጣለች፤ ያንቺም፣ መናር ልበ ቢስ ያሰኝሻ፤ ባለ ውለታሽ ነኝ፤ ከነኛ ጨቁነውና አፍነው ከያዙሽ ወላጆሽ ብለይሽ ዛሬ መወቀስ አለብኝ? በውኑ የምትመዝኝበት ሕሊና የምታስቢበት ልቦና የለሽም? ስወድሽ ባገባሽ፤ ላስጠሽ ብተውሽ ነውሩ እምን ላይ ነው? ኩሊሽ ሆኜ መንገድ በጠረግሁ እወቀሳለሁ? » አላት።

«እንደምትለው ይባል ይሆናል» ብላ እልፍነሽ ልትነግረው ስትጀምር ታደሰ እግሩ አነባብሮ «ሴቶች ታስቃላችሁ ለግል ጥቅማችሁ በግል ሐሳባችሁ ትነሱና» ብሎ ሳይጨርስ እልፍነሽ አቋርጣው ከደረቷ ወደ ታደሰ ጠጋ ብላ ጉብደድ አለችና «ምን ልትል ነው? አንተ አረመኔ፤ በውኑ ለግል ጥቅሜ ነው? ነውን ታደሰ? ንገረኝ» ብትል ታደሰ «ኋላማ ለግሌ ነውን? » ብሎ ተነስቶ ይንጎራደድ ጀመር።

«ተው ታደሰ» አለችው እልፍነሽ «ያኔ ምን አልከኝ? እንዴትስ አባበልከኝ? እንዴትስ እግ» ብላ ሳትጨርስ ታደሰ ቴፕ ሬኮርዱን ከፍቶ እስቲግል ድረስ ባጠግቡ ቆሞ ይመለከተው ነበርና አንገቱን ወደ ቀኙ በጥቂት ዞር አድርጎ «አድምጪ እልፍነሽ» አላት «እንደወንድነቴ

በመጀመሪያ ወደድኩሽ አላምንህ ብትይኝ መኝታ ቤት ግቢና ከኮሞዲኖው ውስጥ የጻፍሽልኝን ወረቀቶች ተመልከች፤ አሁን ዘፈን ልስማበት አታደንቁሪኝ» ሲላት ሁለት ዘለላ እንባዎች በእልፍነሽ ሁለት ጉንጮች ላይ ወረዱ።

(አንደዜ ታደሰ ለእልፍነሽ በጻፈላት ደብዳቤ ላይ አችን ጥሩ ነበርሽ ወዴት ይገኛሽ ልጥፋ» ብሎ ጽፎላት ስለ ነበር እሷ ደግሞ አበኩ፤ ሞትኩ፤ ተቀበርኩ የሚለውን ግጥሟን ከደረደረች በኋላ «- አለባበስህ ተውሳክ ሽሚዝህ ጉዳይ ሽቅርቃሮትህ ጦር ነው ልብ አመሳቃይ

ሞታለች ሰቀለኝ ከረባትህ ላይ - » ብላ ጽፋለት ስለ ነበረ አሁን የተናገራት ያን አስታውሶ ነው መሰለኝ።)

በታደሰ አነጋገር እልፍነሽ አገጯን ተመርኩዛ ተከዘች፤ ባባች፤ ሆድ ባሳት፤ እንዲወርዱ ያልፈቀደችላቸው እንቦች እየተንቆለቆሉ ቀሚሷ ላይ ተንጠባጠቡ፤ ታደሰ ከሳሎን ከረጅሙ ፎቼ ላይ እጆቹን ተንተርሶ እግሮቹን አርግቶና አነባብሮ በጀርባው ጋደም አለ፤ ቴፕ ሬኮርዱ «ኡኡታ አያስከፋም ሲለዩ ተዋዶ» የተሰኘውን ዘፈን ይዘፍናል፤ እልፍነሽ በቁጣ ተነሥታ ወጣች፤ ታደሰ እንደተጋደመ ሳቅ አለ፤ እልፍነሽ እንደ ገና ልጃገረድ ልትሆን ሔደች እኔም አልተከተልኳትም።

# ምዕራፍ ፫

አንድ ቀን ማታ ከእናቴ ከወይዘሮ በለጥሻቸው አንዳርጌ ጋር ተቀምጠን ስለ ዱሮ ወይዘሮዎች መዋረድ ስናወራ በጨዋታ ጨዋታ የተነሣ እናቴ ወይዘሮ አሰገደችን ያውቋቸው ኖር ስለ እሳቸው አጫውተውኛል።

ወይዘሮ አሰገደች ጣሊያን ሀገራችን ከመግባቱ በፊት የነጋድራስ ወልደ ሒሮስ ሚስት ነበሩ፤ ነጋድራስ ወልደ ኪሮስ የአራ ኬላና የአሥር አንድ ገበያ ነጋድራስ ስለ ነበሩ በዚያ ዘመን የነበራቸው ሀብት አለመጠን በመሆኑ ወይዘሮ አሰገደች በሚኖሩበት ሀገር እጅግ የተከበሩ ሀብታም ጨዋ ሴት ነበሩ።

ወይዘሮ አሰገደች ከነጋድራስ ወልደ ሒሮስ አንድ ልጅ ወልደዋል፤ በ፲፱፻፴ ዓ.ም በነጋድራስ ቤት እጃታዋ በዝሆን ጥርስ የተሠራች የወገባቸው ሽጉጥ ስለተገኘባቸው አራዳ መሐል በጥይት ተደብድበው ሞቱ፤ ልጃቸው ወንድወሰንም ለኢጣሊያኖች ተቀጥሮ ባሊላ ተብሎ ስለ ነበረ የደረሰበት አይታወቅም፤ ወይዘሮ አሰገደችም እንደ ሞተ ያህል ቆጥረውታል፤ እርማቸውንም አውጥተዋል።

ወይዘሮ አሰገደች እጅግ አለመጠን የተከበሩትን ያህል ደህይተው ጠላ ይሸጣሉ፤ በተከበርኩበትና በታወቅሁበት ሀገር አዲሳባ ተዋርጄ ከመኖር ብለው ወደ አሰበ ተፈሪ ወርደው ተቀምጥዋል፤ በአሰበ ተፈሪ ከተማ ሁነው ጠላ ሲሸጡ ካንድ ከማይረባ ጠላ ጠጪ ሰው አንድ ሴት ልጅ ወልደዋል፤ ስሟንም ትዕግሥት ብለዋታል።

ወይዘሮ አሰገድች መኮንን ሜዲ ከተሰኘው መንደር ደስ ያለችውን ሣር ቤት በወር ሺሊንግ ተከራይተው ልጃቸውን ትዕግሥትን አሳደጉ የአሰበ ተፈሪን ልጆች እግር ሙጃሌ ስለሚያጠቃቸው የትዕግሥትም እግሮች በሙጃሌ ተተብትበው ነበር፤ አንዳንዴም እናቷ ወይዘሮ አሰገደች ከየእጇዋ ላይ እንኳ ሙጃሌዎች ያወጡላት ነበር አሉ።

ትዕግሥት እንዳቅሚ ተማሪ ቤት ገብታለች፤ ከተማሪ ቤት ስትመለስ በቤት ውስጥ እናትየዋን ሥራ ተረዳለች፤ ከመንደሯ ልጆች ጋር ልጫወት ብትል እንኳ ልጆቹ እየናቋት ያባርሯታል፤ ወደ ማታ ገደማ የሚሸጥ እንጀራ ከጉልት ወስዳ ትሸጣለች የጠጅ ሻጪ ልጅ አሰለፈች እንኳ እንዳቅሚ ትዕግሥትን አዘውትራ «አንቺ እንጀራ ሻጭ የእንጀራ ጋጋሪ ልጅ» ታልት ነበር፤ የሷን ተከትለው ትንንሾቹ ልጆች ሁሉ ትዕግሥትን ይሰድቧታል።

አንድ ጊዜ እኔ ወደ አሰበ ተፈሪ ወርጅጄ ነበር፤ ካረፍኩበት ሆቴል ቤት ከጀግኖች ማኅበር ፎቅ ላይ ሁኜ ወደ ማታው ገደማ የሚተረማመሰውን መንገደኛ ቁልቁል ስመለከት ትዕግሥት በሰፌድ እንጀራዋን ተሸክማ አንድ አዳፋ ነጠላ ሸፍናው የተቀዳደደ ቀሚሷን ለብሳ ሸፈፍ ሸፈፍ እያለች ወደ ገበያ ስትሔድ አየኋት፤ ልጅቷ ደመ ግቡ ስለ ነበረች መልኳ አስደነገጠኝ።

ወዲያውኑ ከፊት ለፊት ካለው የእስላም ሆቴል ቤት እንጀራዋን ሽጣ ስትመለስ ተከተልኳት፤ አብሬአት ከቤትዋ ገብቼ አንድ ጣሳ ጠላ አስቀድቼ በኩራዝ መብራት ስናወራ አመሸንና ለናትየዋ አምስት ብር ሰጥቻቸው ተመለስሁ፤ ትዕግሥት ደስ ብላኝ ወድጃት ነበር፤ ካረፍኩበት ሆቴል ለማውቃቸው ሰዎች ባማከራቸው «ዘረ ቆማጣ ና፤ የዓረቡ ሁሉ መጫወቻ ና፤ ሥራው በየሻዩ ቤት መደፋት ነው፤ ሊስትርዎ ሁሉ ወዳጅዋ ነው» እያሉ ጣጣዋን ስላበዙብኝና ያሏታ ሁሉ ሐሰት መሆኑ ቢሰማኝም ልቤ እየወደዳት በይሉኝታ ተውኳት።

//=//

አዲስ አበባ በመጣሁ ልክ ፪ ዓመቴ የሚካኤል ለታ እንዳለፈ ከፒያዛ ካለው ከአንድ ከወዳጄ መድኃኒት መሸጫ ቤት ተቀምጬ ስናወጋ ተረከዘ ክፍቱን ነጭ ቡሽ ጫማ ያደረገች ቡናማ መልክ ያለው ፓሪ ሞድ የለበሰች፤ ትልቁን ባለ ማንጠልጠያ ነጭ ቦርሳ የያዘች፤ ዞማው ጠጉርዋ አለ መጠን ያስዋባት ልጅ ከሱቁ ገብታ ሞዴስ (MODESS) ይስጡኝ አለች፤ ወሬአችን ሳናስበው ተቋረጠ፤ ሁላችንም ፈዘን አየናት፤ አብሶማ እኔ ድርቅ አልኩባት፤ ሻጩ እንኳ ሞዴሱን ሲሰጣት ፈገግ ያሰኘው አንድ አዚም የነካው መሰለን።

ሞዴሱን ገዝታ ስትመለስ ዓይታኝ ሳቅ አለች፤ አጥንቴ አልተገነጣጠለም እንጂ ካለሁበት ቦታ ፍርክስክስ አልኩ፤ ጠጋ ብላ ጤና ይስጥልኝ ብትለኝ ምላሴ እንደ እግሬ ተብረከረከ፤ ላብ አሰመጠኝ፤ ብብቶቼ ጋሉ፤ ትኩሳት ተነሳብኝ፤ «አውቅሃለሁ» ባል የት እንደምንተዋወቅ ብትነግረኝ የአሰበ ተፈሪዋ ትዕግሥት ሆና አገኘኋት እዚያ መሐል መጫወቱን ጠልታና ጠልቼ ይዣት ወጣሁ፤ አብሬአትም ጥቂት አዘገሁ።

ቡና ቤት ቡና ልጋብዝሽ አልኳት፤ እሺ ብላኝ ገባን፤ ከዚያም ሆነን እንዴት ከዚህ እንደደረሰች አጫወተችኝ፤ «ሥራ አልያዝኩም» አለችኝ፤ «ሥራ በምጠይቅበት መሥሪያ ቤት ሁሉ በደስታ ይቀበሉኝና የምቀጠርበትን ደሞዝ ነግረውኝ ሥራውን እንድንሰጥሽ ጉቦ ስጪን ይሉኛል» ብትለኝ «ታዲያ ለምን አትሰጪያቸውም» አልኳት ፍዝዝ ብላ ወደ ውጭ እያየች «አይይ» አለች፤ ያው ድህነቷ ስላለቀቃት ገንዘብ አጥታ ይሆናል ብዬ «ገንዘብ ይቸግርሽ እንደሆነ እኔ ልርዳሽና ስጫቸው» ብላት

«ገንዘብ አይቸግረኝም፤ ጋሽ ደበበ ለማዩ ፵ ብር ለኔ ፴ ብር ይሰጠናል፤ እንቀርሻለን የሚሉኝ ገንዘብ የሚፈልጉ ቢሆኑ ኖሮ ይቻልኩትን ያህል በሰጠኋቸው እነሱ ግን ጌቶች........» አለችኝ።

ይህን ዓይነቱን የቀጣሪዎች ተግባር ከዚህ በፊት ያልሰማሁ ስለ ነበርሁ ደነቀኝና ጥቂት ካሰላሰልሁ በኋላ «ልጃገረድ ነሽ እንዴ? » አልኳት «የለም ጋአሽ ደበበ ከልጅነቴ ጀምሮ እየረዳኝ ስላስተማረኝ ዛሬም የተቀመጥኩ በሱ ሒሳብ ነው» አለችኝ፤ «ታዲያ ምን አሰጋሽ? » ብላት «ጋሽ ደበበ ለዚህ ያበቃኝ እኔ ያሰበ ተገሪዋ ትዕግሥት ያሁኗን የአዲስ አበባዋን ትዕግሥት አልሆንም ነበር፤ ጋሽ ደበበ ባለውለታዬ ነው፤ እወደዋለሁ፤ እሱም ያምነኛ፤ እግዚአብሔር ባለ ጊዜ ስራ ያሰጠኝ እንጂ ታማኝነቴን አላፈርስም፤ አንተም የአሰበ ተፈሪው ባለውለታዬ ነህና እስቲ በናንተም መሥሪያ ቤት ሆነ በሌላ ዘንድ ሥራ ፈልግልኝ» ብላኝ እየደለች እንድታስታውሰኝ የስልክ ቁጥር ሰጥቻት ተለያየን።

//=//

አንድ ሁለት ውር ያህል ሥራ ስፈልግላት ከረምሁ እሷም፤ ስልክ እየደወለች ታስታውሰኝ ነበር፤ ሥርውን በምጠይቅላት ቦታ ሁሉ «መታ ትንገረ፤ እኛም እንያት» የሚሉኝ ጥቂቶች አልነበሩም፤ በኋላም እግዚአብሔር ይስጠውና አቶ ለማ ሊቀጥራት ተስማማንና ትዕግሥትን ብፈልግ ጠፋችብኝ።

ቤትዋን አላውቀውም አድራሻዋንም አልነገረችኝም ነበር፤ ፲፰ ቀናት ሙሉ ፈልጌ ስላጣኋት ያለመገኘቷን ላቶ ለማ ብነግረው «ቅላ ገብቼልሃለሁና መሰሏን ቆንጆ ሴት በቦታዋ አስገባ» አለኝ። «ኧረ አላገኝም» ብለውም «ላንተ ስል የመጡትን ሁሉ መልሼ አሰናክለሃልና አሁንም አንተው ፈልገህ ማምጣት አለብህ» አለኝ።

ባስታውስ የአክስቴ የወይዘሮ ትደነቂያለሽ ልጅ አልማዝ ታወሰችኝና ባመጣለት «ይቺ እነቅልፍ የምታስመጣ አስቀያሚ ናትና አልቀጥራትም» አለኝ። ስለሚስትነት ያጫኋትን ደመ ግቡ ለሥራ ስፈልግ ከረምሁ።

ሰባት ወራት ያህል ከትዕግሥት ጋር ሳንገናኝ ከረምን፤ የጥምቀት ለት ጃን ሜዳ (ዝሆን ሜዳ ጃን ማለት በአማርኛ ዝሆን ማለት ነው)

እየተዘዋወርኩ ዘፈንና ቆን ሳማርጥ ትዕግሥት ግጥም አለችኝ ለጊዜው ረስቻት ደንገር አለችኝ፤ በኋላ ግን ሳቅ ስትል በጥርሷ ፍንጭት አወኳት።

ጉስቁልቁል ብላለች፤ ልብሷም አልባሌው ሱቲ ነው፤ ጫማዋም እንደ ነገሩ ነው፤ ጠጉርዋን በሻሽ ሸፍናዋለች፤ መልኳ ገርጥቷል፤ ፊቷም ነብዟል፤ ከቁጭምጪምቷ እስከ ቋንጃዋ በላይ አመድ መስሏል፤ ክርንና ክንዷ ውርጭ ያደረበት ይመስላል፤ በጠቅላው ያዲሳባዋ ትዕግሥት እንደ አሰበ ተፈሪዋ ልትሆን መንሻፈፍ ቀርቷታል።

«ምን ሆንሽ? » አልኳት፤ «ደህና ነኝ» አለችኝ፤ «ስራ አልያዝሽም? » ብላት «ይገፐለሁ» አለችኝ «ከየት» ብላት «እንዲህ ወደ ታች ነው» አለችኝ፤ «ከየትኛው መሥሪያ ቤት? » ብላት «ከትራፊክ ክፍል ገቢና ወጪውን ሒያጅና ተመላሹን ሁሉ መዝጋቢ ሆኛለሁ» አለችኝ፤ «ይህ ምን ዓየንት አዲስ ሥራ ነው? » ብላት «ሥራው ኗሪ ነው፤ ብቻ የኔ ታሪክ በቀላሉ አያልቅም፤ እንዳጫወትህ ብትፈልግ ከዚህ ከግርግሩ መሐል እንውጣ» አለችኝ፤ እኔም መቼም በሴት ልጆች አልጨክንምና ባገኝ እጠልፋለሁ ባጣ እመለሳለሁ ብዬ የሔድኩበትን ጉዳይ ትቼ ከትዕግሥት ጋር ወዳንዱ ድንኳን ገብተን ምሳዋን ገዝቼላት በላን፤ ቢራምን ጠጣንና ወጣን፤ ከዚያም በኋላ ከወደታች ካለው አጥር አጠገብ ሔደን ከዛፎቹ ጥላ ሥር አርፈን እኔ ክንዴን ተመርኩዤ ገደም አልኩ፤ ትዕግሥት ቀሚሷን ጎዝጉዛ ካጠገቤ ቁጭ አለች፤ ለጊዜው የገዛሁላትን ከረሜላና መስቲካ እየበላች ወሬ ጀመረችልኝ።

«ያን ጊዜ አንተን ካገኘሁህ ወዲህ አንድ ጋሽ ኃይሉ የምንለው ሰውዬ ሥራ ወዳለበት መሥሪያ ቤት ወሰደኝ፤ ከዚያም ከሹሙ ጋር ተገናኘሁና በአቀባበላቸው ደስ አሰኙኝ፤ የሥራ ችሎታዬን ሳይጠይቁኝ የወር ደሞዜ መነሻ ፩፻፸፭ ብር እንደሚሆን ነገሩኝ ደስ አለኝ፤ ነገ ተመለሺ ብለውኝ ሔድኩ በነጋታው ያለ ምን ሐተታ ተቀጠርኩ።

«በተቀጠርኩ በ፫ኛው ቀን አለቃዬ ማንትስ ከሚባል ሆቴል ቤት እሑድ እጠብቅሻለሁና እንድትመጪ አሉኝ፤ ምን አረጋለሁ? ብላቸው አዝገቼሻለሁ፤ አሉኝ ነገሩን ለጋሽ ደበበ ባማርከው በእረፍ ቀንሽ ሊያዝሽ አይችልምና አትሒጂ አለኝ ሰኞ ለታ አለቃዬ ተቆጡኝ ከደሞዜ ፲፭ ቀን እንዲቆረጥ ማዘዣ ጻፉ።

«በሳምንቱ ቅዳሜ ጧት ደግሞ «ነገ ካልኩሽ ቦታ ድረስ ባትመጪ ወዮልሽ» ብለው ሔዱ ለጋሽ ደበበ ነገርኩት የተቆረጠብኝን ገንዘብ በአጠፌታው ፴ ብር አርጎ ሰጠኝ፤ እንዳልሔድም አስጠነቀቀኝ፤ ሰኞ ዕለት አለቃዬ በጣም ቢቆጡኝ «እናቴ ታማብኝ ነው የቀረሁት» ብያቸው ሳይቆጡኝ ቀሩ።

«ማክሰኞ ለታ «ሥራ ስላለ በሰዓት ወደ ቤትሽ እንዳትሔጂ» አሉኝና ዋልን፤ በስምንት ሰዓት ላይ እንሒድ ብለው ስንወጣ ላድርስሽ አሉኝና በቮልስ መኪናቸው ይዘውኝ ከነገሩኝ ሆቴል ቤት ወሰዱኝ ለግዜው ባቅማማም አለቃዬ ስለሆኑ አላንገራገርኩም፤ በዚያም ሆቴል ቤት እስከ ፲ ሰዓት ድረስ ዘገየንና ስንመለስ ሆቴሉ ቤት በነበርን ጊዜ መሐረቤን ከቦርሳዬ አውጥቼ ፍራሹ ሥር ረስቼው ስለ ነበር እንደ ገና ለመሐረቡ ሥል ተመለስንና እስከ ምሽቱ ፩ ሰዓት ድረስ አመሸን።

«እቤት ስገባ ጋሽ ደበበን አገኘሁት፤ እናቴም ተጨንቃ ደረስኩባት፤ «የት ውለሽ አመሸሽ? » ቢሉኝ «የይልፋሸዋ ማኅበር ዛሬ ስለነበር ምሳም እዛው በላን ማታ ደግሞ እንዳትቀሩ ብላን ነበርና ከጓደኞቼ ጋር ሔጄ አለቅ ብላ አስመሸችኝ አልኳቸው።

«ጋሽ ደበበ ሳይቆጣኝ ሔደ፤ ለሊት ከእናቴ ጋር ተኝተን ጉዳዩን ባጫውታት አዘነች፤ ደበበ እንዳይሰማና እንዳያይም አስጠነቀቀችኝ፤ ሆኖም እኔ ልጅዋ ለዚህ በመብቃቴም ደስ አላት፤ «ገና እስተዋንዮው ትደርሽበታለሽ አለችኝ»።

«አለቃዬ ወደዱኝ፤ እኔም ወደድኳቸው፤ አንዳንዴም በቢሮ ውስጥ መሳሳም ጀመርን፤ አንድ ቀን ለታ እንኳ ያ ገብረ ወልድ ደብዳቤ ሊያስፈርማቸው ዘው ቢል እላያቸው ላይ ተቀምጬ አየን፤ ለካንስ በሩን ረስተን አልቆለፍነውም ኖርዋል።

«አንድ ቀን ለታ ማታ እስተምልክቱ የእስጢፋኖስ ለታ ከለመድንበት ሆቴል ቦት ስንገባ ብርድ ልብስ የተከናነበው ዘበኛ ለት ብሎ እጅ ነሳን፤ እሳቸውም አንድ ብር አውጥተው ሰጡት፤ እኔ ግን ሰው እንዳያየኝ ሮጪ ገባሁ፤ ከምሽቱ ፫ ሰዓት ላይ ስንወጣ አይው ዘበኛ እንደ ገና እጅ ነሥቶ ጥቂት ሸኘንና መኪናችን አጠገብ ልንደርስ ስንል ተመልሰ፤ መኪና ውስጥ ልንገባ ስንል ዘበኛው እየሮጠ ተመልሶ መጣና፤ «እሜትዬ አንዴ

እፈልጐታለሁ» አለኝ «ለምን? » ቢሉት «የረሱት ዕቃ አለና ገብተው ይውሰዱ» ቢለኝ ደንግጬ ስሮጥ ገባሁ።

«በአልጋው ስር አጎንብሼ ስፈልገ ዘበኛው መጣና «አጡት እንዴ» አለኝ፤ «አዎ አልኩና ዞር ስል ባየው ብርድ ልብሱን ተገለጠ፤ አለመጠን ደንግጬ ወደቅሁ በኋላ ነፍሴን አውቄ ተንሰራርቼ ስነሳ ካጠገቤ አጣሁት።

«አለቃዬ ከበኢቴ አደረሱኝ፤ እቤትም እንደ ገባሁ እናቴ «ይህን ብርድ ልብስ ደበበ ስጫት ብሎኛል» ብላ ሰጠችኝ፤ ባየው ጋሽ ደበበ ዘበኛ እምስሎ ካስተናገደኝ በኋላ «አጡት እንዴ? ብሎኝ ሲገለጥ ያወቅሁት ጊዜ ለብሶት የነበረ ዝንጉርጉር ብርድ ልብስ መሆኑን አወቅሁና አለቀስሁ፤ እናቴም አፅናናቺኝ እግዚአብሔር ሲከስትብኝ ያን ለታ ብቻ ቀበጥ አርጎን ማታ ሔድን እንጂ ለወትሮአችን በሥራ ሰዓት ነበር የምንሔደው።

«በነገታው ጉዳዩን ለአለቃዬ ዘርዝሬ ነገርኳቸው፤ ደበበ ቢቀር ምንም ዓይነት ችግር እንደማይደርብኝ ነገሩኝ፤ ሊረዱኝም ቃል ገቡልኝ ሚስታቸው ሊያረጉኝም ተስፋ ሰጡኝ፤ ጋሽ ደበበን ናቅሁት፤ እስተመፈጠሩም ረሳሁት፤ አለቃዬን አግብቼ ያለቃዬን ሥልጣን የጨበጥሁ መስለኝ፤ ጋሽ ደበበ «ለዚህ አበቃሁሽ፤ የነጠቀኝ ያዛልቅሽ፤ ከኔ የበለጠብሽ ያኑርሽ ለብዙ ግዜ ሳልንቅሽ በጥቂጥ ቀን ናቅሺኝ፤ ልቤን ሰጥቼሽ አፍ በልጦብሽ ተውሺኝ፤ ደህና ሰንብቺ የሚሉ አነጋገሮች ያሉበት ደብዳቤ ጻፈልኝ፤ ከበርደም ላረኩት እስተነአካቴው ነዶኝ ላለቃዬ ብነግራቸው ተናደው ዛቱበት።

«ካለቃዬ ጋር ነፈስሁ፤ ደበበ እግረኛ ነበር፤ አለቃዬ ግን መኪነኛ ናቸው፤ በውነቱ አብሮ እንትን ማለት ያናንቃል እንደሚባለው አክብራቸው የነበሩትን አለቃዬን ናቅኋቸው፤ ከጋሽ ደበበ ጋር ከተለያየን ከ፪ ወር በኋላ በማይረባ ነገር ከአለቃዬ ጋር ተቀያየምን፤ ካንገቴ በላይ ላኮርፍ ብቃጣ አምርረው አኮረፉኝ፤ እንደናቅኋቸውም ናቁኝ፤ ፊት ነሱኝ በተኳረፍን በስምንተኛው ቀን ከሥራ የተሰናበትኩበት ማዘዣ ሳላስበው ደረሰኝ፤ ለግዜው ሳልደነግጥ ተናድጄ እየተሳደሁ ሥራዬን ለቀቅሁ፤ በኔም ቦታ ፈትለ ወርቅ የተባለች ልጅ ተቀጠረች፤ እሷም እንደኔው ሆና ወጣት

ከሷ በኋላ የተቀጠረችው አበበች አንድ ቀን ተገናኝተን ስታወራልኝ እንደኔው ሆኑ መሰለህ።

«እኔም ሥራ ብፈልግና ባፈላልግም አጣሁ፤ የነበረኝ ቅርስ አለቀ፤ ከእናቴ ጋር የምንሆነው ስለጠፋን ከቁራጭ አንድ በኢት በ፳ ብር ተከራይቼ ቀይ መብራት በማብራት የእግረኛ ትራፊክ ሆኛለሁ።

«በዚያ በቁራጭ ጋሽ ደበበ በመኪና ሲያልፉ ሁሌ ያየኛል፤ አያነጋግረኝም፤ ስለቅለትም ዝም ብሎኝ ያልፋል ታሪኬ ይሔ ነው፤ ይህ አሁን የጀመርኩት ሥራ እማያዋጣኝና እማልዘልቀውም ነውና እባክህ ካንተም ቤት ቢሆን ቅጠረኝ» አለችኝ።

«እኔም እንዲች ዓይነትዋ ሴት ከቤቴ ብትገባ ዓመሏን ለዛሬ ታጋባለች ብዬ ጠላኋት፤ እይሚያምረውም መልኳ አስቀየመኝና «ወይ ሰው ዓይኗ ጥርሷ ተረከዝ መልካም

ይሉሽ የነበረ፤

መልክ እንዲህ ይጠፋል ዓመል ካላማረ፤

እንዲህ ውብ ልጅ ሆኖ መልክ ከማማር

ግማሹ ቁም ነገር ቢሆን ምን ነበር»

ብዬ እናቴ ይነግሩኝ የነበሩትን ግጥሞች ገጣጥሜላት «እንዳልቀጥርሽ አዲስ ባለሞያ ገረድ አሁን በቅርብ ቀጠርሁ፤ ቀላቢዬም እናቴ ናቸው፤ ከጎረቤት የሆቴል ተቀላቢዎች ወንደላጤዎች ስላሉ ምናልባት ቢፈልጉ እጠይቅልሻለሁ» አልኳት።

«እንግዲያስ እየመጣሁ እንድጠይቅህ ቤትህን አሳየኝ» ብትለኝ «እኔ እግረኛ አንቺ የእግር ትራፊክ ዘበኛ እንዴት ልንዛመድ እንችላለን? ብቻ በመላው ቤትሽን አውቄዋለሁና ሳገኝልሽ ብቅ ብዬ እነግርሻለሁ» አልኳት

ትዕግሥት ሳታስበው እንባዋ ዱብ ዱብ ዱብ «ይህ ሁሉ የጋሽ ደበበ ጡር ነው» አለችኝ፤ «ይህን በፊት ብታስቢው ጥሩ ነበር» አልኳትና «ለመሆኑ አለቃሽ ማን ይባሉ ኖርዋል? » ብላት ከሚዳው ሥራ አንዷን ረዘም ያለችዋን ነጬት አድርጋ በትርሷ እየከረታተፈች «አቶ ታደሰ ወልደ ማርያም ይባላሉ» አለችኝ።

# ምዕራፍ ፬

የአባቴ እህት እመት አባይነሽ አቶ ገብረ ጊዮርጊስን አግብተው ጉለሌ ይኖሩ ስለ ነበረ፤ እሳቸውን ለመጠየቅ ወደ ጉለሌ ስመላለስ ተዋበችን አውቃታለሁ፤ የአክስቴ የእመት አባይነሽ ልጅ በለጠ የተዋበች ጓደኛ ስለ ነበር ስለ ተዋበች ሁልጊዜ ያጫውቱኝ ነበር፤ አክስቴ እንኳን ተዋበችን እንጭልህ ብለውኝ የበለጠ የከንፈር ወዳጅ ስለ ነበረችኝ ነገሩን ሳልገልፅ በደፈናው እንቢ ብያቸዋለሁ።

ተዋበች የተወለደችው አዲሳባ ከተማ አራት ኪሎ ነው፤ ለጥቂት ጊዜ ቀበና ኖራለች፤ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፩ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ ፲ኛ ክፍል ተምሬአለሁ ትላለች፤ የተዋበች ወላጅጆች ብዙ ልጆች ወልደዋል፤ ከወለዷቸውም ልጆች መሐል ተዋበች ብቻ ሻል ያለች ቆንጆ ነች፤ ተዋበች በዝርዋ የጠራች የጨዋ ልጅ ነች።

የተዋበች ወላጆች ተዋበችን ስለሚያከብሯት ዘለዘል አድርገዋታል፤ የምትሠራውም መጥፎ ነገር ሁሉ ጥሩ ይመስላቸዋል፤ ተዋበችን አታውቋትም፤ መሰለኝ ተዋበች አጭር ናት፤ ቀልቃላ ናት፤ አንዳንዴ እንኳ የወንድ ሱሪ ትታጠቃለች የተዋበች ፊት እንደኳስ የተድበለበለች ትንሽ አንት፤ ተዋበች ጠይም ናት፤ አፍንጫዋ አጭር ናት፤ ተዋበችን ስታይዋት ደስ ትላችሁና ብልግናዋ ያስጠላችኋል፤ ዘሮችዋም በብልግናዋ የሚደሰቱ ስለሆኑ፤ እሷም ጥፋቷ አይታወቃትም።

ተዋበች መሳቅ መሽኮርመምና መገርመም ታበዛለች፤ ይህም ቢሆን ተዋበች ከትምህርት ቤት ከንፈር ወዳጆችዋ ጋር መሳሳምን ትወዳለች እንጂ እስከ ፲፬ ዓመቷ ጥንቁቅ ነበረች። አሳሳም እንኳ ስለማታውቅበት ወንዶቹ ልጆች የከንፈር ወዳጅ ነገር አንስተው ሲያወሩ በተዋበች አሳሳም ይስቁባት ነበር፤ ከትምህርት ቤቱ ልጆች መሐል የተዋበች የከንፈር ወዳጅ ያልሆኑ ጥቂቶች ናቸው፤ ታዲያ ከሁሉም ልጆች አብልጦ የሚወዳትና አሳሳሟም ልቡም የሚያጠፋው ገብረ ሥላሴ ነበር፤ አገባሻለሁ ብሎ እንኳን ተፋ ሰጥቷት ነበር።

ታደሰ ለሽርሽር ወደ ጉለሌ ሲሔድ ተዋበች ሜዳ ላይ ስትዘል አያት፤ ደስ አለችው ደንገጠባት፤ ሁኔታዋንም ጠይቆ ተረዳ፤ ታደሰ ከተዋበች

አባት ካቶ የተመኙ ጋር ተዋወቀና ተወዳጃቸው። ታደሰ እተዋበች ቤት እየሔደ ኮርኒስ በሌለው ቆርቆሮ ጣርያ ሥር ካቶ የተመኙ አልጋ አጠገብ ካለችው ሣጥን ላይ ቁጭ ብሎ ይውል ጀመር፤ የታደሰ ቮልስ ዋገን ከደጅ መቆምም የተዋበችን ወላጆች አስኮራቸው።

አንድ ቀን የተዋበች ወላጆች ችግር ገጥሟቸው ወደ ጎንደር ሔዱ፤ ቤታቸውን ለታደሰ አደራ አሉት፤ ለልጆቹ ምግብ አብሳይ ወልተ ሒሮስን ገረድ ቀጥረው ሔዱ፤ ታደሰ ደስ ብሎት አደራውን ተቀበለ፤ ሁለት ቀናት ያህል ያቶ የተመኙን ማቲዎች ታደሰ ሲያንሸራሽር ዋለ በ፫ኛው ቀን ታደሰ ተዋበችን ይዟት ወጣ፤ ብስኩት ገዛላት፤ ተዋበችም ደስ አላት።

ታደሰ ተዋበችን «እወድሻለሁ እኮ» ቢላት ተዋበች ቀለስለስ ብላ «ኡ የኔን ያህል አትወደኝም» አለችው፤ ታደሰ በቀጥታ ወደ ቤቱ ወስዶ ጋበዛትም ጥቂት ሲሳሳሙ አመሹ፤ ያልሠለተነው የተዋበች አሳሳም ታደሰን ልቡን አጠፋው ከመኝታ ቤት ይዟት ገባ፤ ተኙ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተዋበች አንደዜ ዋይ ብላ ዝም አለች በነገታው እንደነበረች አልብሶ እንደነበረች ሳትሆን ወደ ቤትዋ ወሰዳት ወለተ ሔሮስ ጉዳዩ ቢገባትም ዝም አለች የአፍ መለጎሚያም አገኘች። ገረዲቱ ወለተ ሒሮስ ለእመቤቷ ለተዋበች እመቤት ሆነች።

የተዋበች ወላጆች መጡ፤ ሳይሰሙ ቆዩ፤ ተዋበች አረገዘች፤ ወላጆችዋ አሰቡ እንጂ አልደነገጡም፤ ተዋበች «ጋሽ ታደስ እንዲህ አረገኝ» ብላ ነገረቻቸው፤ ሳይነዳቸው ታደሰን ከሰሱት፤ በሽማግሌ እርቅ ጠየቀ፤ ለጊዜው ሃምሳ ብር ሰጣቸው፤ የተዋበች ወላጆች ተደስተው ተመለሱ።

የተዋበች ሆድ እየገፋ ሔደ፤ ተዋበች ዘጠኝ ወር ሞላት ከልዕልት ጸሐይ ሆስፒታል ገብታ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ታደሰ ሁለት ቀን ያህል ተመላልሶ ጠየቃትና የአምስት ቀን የሆስፒታል ሂሳብ ከፍሎላት «ከእንግዲህ ወዲህ እንደፈለግሽ ሁኝ» አላት፤ ተዋበች የምትከፍለው ስለሌላት በስድስተኛው ቀን ከሆስፒታሉ ቤቶቿ ሳይሰሙ ወጣች፤ ልጅዋን ከታደሰ የወለደችውን ታደሰ ሊያሳድገው ያልፈለገውን ይዛ ከሠፈርዋ መግባት ስለ ፈራችና ስለጠላች፤ ከዱር ትታው ስትሔድ የልጁ ዋይታ እያባባት ስትመለስና በላዩ ላይ ሆና ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ የመንደርዋ

የጉለሌ ሰዎች አዩዋት፤ ከነልጅዋ ይዘው ወደ ቤትዋ ወሰዷት፤ ተዋበችን ታደሰ መቅኖ እንዳሳጣት ልጅዋም በተወለደ በሦስት ወሩ ሞተ።

ላልሰማው መታፈሪያ ልጃገረድ ናት ተብላ ቀለበት አድርጋ በሠርግ ተዳረች፤ ያዳቆነ ሠይጣን ሳያቀስስ አይተውም እንደሚባለው ተዋበች ከመታፈሪያ ጋር በአምስት ወር የጋብቻ ዕድሜያቸው አሥራ አራት ጊዜ ተጣልተው በ፲፫ኛው ጥቅምት ፱ ቀን ተፋቱ ዛሬም ተዋበች በልጃገረድ ስም ቤት ተከራይታ ተቀምጣለች።

# ምዕራፍ ፰

ኃይለ ማርያም በአገር ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ ይሠራል ኃይለ ማርያም በየወሩ ፫፻፶ ብር ያገኛል፤ ኃይለ ማርያም አጠር ያለ ቀይ ዳማ ነው፤ የኃይለ ማርያም አንፍጫ አጠር ያለ ቢሆንም የደስ ደስ ያው ደማም ነው፤

ኃይለ ማርያም በጄነራሉ ዊንጌት ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አከናውኖ የተመረቀ ነው፤ ኃይለ ማርያም በአገር ግዛት ውስጥ ለ፳ ዓመታት ያህል አገልግሏል፤ የኃይለ ማርያም ባሕርይ የነጠረ በመሆኑ ከተላላኪ ጀምሮ እስከ ዋናው ሚኒስትር ድረስ ይወዱታል።

ኃይለ ማርያም ቤቱ ጉለሌ ነው፤ ኃይለ ማርያም ቦታው የጭሰኝነት ሆኖ መልካም ቤት ሠርቷል። የኃይለ ማርያም ቤት አጠር ባለ የግንብ አጥር የተከበበ ነው፤ በግንቡ ላይ ፍርግርግ የብረት አጥሮች አሉ፤ በግቢው እጅግ ብዙና በአስተካከላቸው የሚያማምሩ አበቦችና መስኮት አሉ፤ በመስኮቶቹና በአበቦቹ እምሐል አንዲት የአየር መቀበያ ግድግዳ የሌላት ሣር ቤት አለች፤ በዚያችም ቤት ኃይለ ማርያም ከሚስቱ ከአስቴር ጋር ሲጫወቱና ሲወያዩ ያመሻሉ።

አስቴር የደስ ደስ ያላት ፉንጋ ናት፤ ቁመቷ ረዘም ያለ በመሆኑ ሸንጣማና ዳሌያም ናት፤ አስቴር ያያት ወንድ ሁሉ የማይወዳት ነብረች፤ ኃይለ ማርያም ግን ትዳር ፈላጊ በመሆኑ «ትሆነኛለች» ብሎ አግብቷት ሁለት ወንዶች እና አንዲት ሴት ልጅ ወልዳለታለች።

አስቴርና ኃይለ ማርያም እጅግ በጣም ይዋደዳሉ፤ ማታ ተኝተው መብራት አያጠፉም፤ አስቴር ስታየው ዓይኗን ደከሟት ያሽልባታል፤ ኃይለ ማርያምም በስልምልም ዓይኑ እንዳያት ሳያውቀው ያንቀላፋል፤ ጎህ ሲቀድ ነቅተው የማታ ቁራጭ ወሬአቸውን ይቀጥላሉ፤ አብዛኛውን ጊዜ የነግህ ወሬአቸው «ኃይልዬ በሕልሜ ካንተ ጋር እንዲህ እንዲህ ስናደርግ አየሁ» ስትለው እሱም ደግሞ «እኔም አስቴርዬ በሕልሜም ካንቺው ጋር አደርኩ» የመሳሰሉ ነበር።

በነግህ ከሕልም ውይይታቸው በኋላ አስቴር ዘዬ ብላ የያዘችው ካንገቷ ቀና ብላ ቁልቁል እያየችው «ኃይልዬ? እኔ እኮ በሕልሜ ስትስመኝ አይቻለሁ፤ አሁን በላ» የሚሉትን አነጋገሮች ነበር፤ ኃይለ ማርያም የአስቴር የነግህ ትንፋሿ መዓዛ አያስቀይመውም፤ ልጋጓ የወረደበት የአስቴር የጧት ፊት አይቀፈውም ይወዳታል።

አስቴርም ብትሆን የሲጃራ ጠጪው ባሏ የጧት ትንፋሽ አይከረፋትም፤ በከንፈሩ ላይ ሰፍረው የምታያቸው የሞቱ ቆዳዎች አያስቀይሟትም፤ ታፍኖ ያደረው የብብቱ መዓዛ አይቀረናትም በስተቀኝ ፊቱ ካፉ ጀምሮ የተሰመረው ነጭ መስመር አስቴርን አያቅለሽልሻትም፤ የዓይኑ ላይ ቅምጦች አያስከፏትም፤ ትወደዋለች።

አስቴር የምትሠራው ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፤ ማለዳ ተነስተው ፊታቸውን ታጥበው ልብሳቸውን ለብሰው ቁርሳቸውን በልተው ባለቻቸው ታኑስ መኪና ሦስቱን ልጆቻቸውን ከኋላ አድርገው ኃይለ ማርያም እየነዳ አስቴር ከጎኑ ተቀምጣ መጀመሪያውን ናዝሬት ተማሪ ቤት ይሔዱና ሦስቱንም ልጆቻቸውንም ሳስመው ከተማሪ ቤቱ ትተዋቸው ወደ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሔዳሉ፤ ከዚያም ከግቢው ውስጥ አስቴር ከመኪናው ልትወርድ ስትል ማንም ቢያያቸው ሳያፍሩ ከንፈሮቻቸውን አጋጥጭው ይለያያሉ፤ የአስቴር ጓደኞችም እየቀኑበት «እንዲያው ልጅዬ፤ መች ይሆን ሲሏት ደስ እያላት ትኮራለች፤ ፲ ዓመታት ሙሉ የመመላለሳቸው ተግባባ ይሔ ነው።

አሰላ ከተማ ያሉት የኃይለ ማርያም እናት ታመው ኃይለ ማርያም ተጠርቶ ሔደ፤ አስቴር እንኳን እሔዳለሁ ብላ አስቸግራ ለልጆቹና ለቤቱ ስትል ቀረች።

ኃይለ ማርያም መኪናውን ይዞ በመሔድዱ ልጆቹን ወርቁ የተባለው አሽከር ቦርሳቸውን ጀመር አስቴርም ከጉለሌ ፒያዛ ድረስ በ፮ ቁጥር ከዚያም ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ድረስ በ፱ ቁጥር አውቶብሶች ትመላለስ ጀመር።

አንድ ቀን ለታ በ፯ ሰዓት አስቴር ከ፮ ኪሎ በታች ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ፊት ለፊት ቆማ አውቶብስ ትጠብቃለች፤ ታደሰ በተዋበች ምክንያት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሎ ለተዋበች አባት ላቶ የተመኙ ሃያ ብር ሰጥቶ ተገላግሎ ሲመለስ አስቴርን ቆማ አያት፤ መኪናውን ካጠገቧ አቁሞ ጤና ይስጥልኝ ቢላት ሰድባ አዋረደችው፤ አስቴር ለባሏ ታማኝ ናት፤ አስቴር እንደ ጓደኞቿ አይደለችም፤ አስቴር ጨዋ ናት፤ አስቴር ባሏን አኩሪና አስከባሪ ናት፤ አስቴር ትዳሯን ወዳድ ናት፤ አስቴር ከኃይለ ማርያም ሌላ ወንድ ያለ አይመስላትም፤ ኃይለ ማርያም ዕድለኛ ነው።

ያን ለታ ታደሰ አፍሮ ሔደ፤ ልክ ለዘጠኝ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በር ላይ በእግሩ ቆሞ ሲጠባበቅ ሳለ፤ አስቴር ካውቶብስ ስትወርድ አያት፤ ስትገባም ተከትሏት ከቢሮዋ ገብቶ ባለ ጉዳይ መስሎ በሐሰተኛ ጉዳይ አስቴርን ሲያለፋት ዋለ፤ አስቴር እርግጠኛ ባለ ጉዳይ መስሏት ካንዱ ቢሮ ወዳንዱ ቢሮ እየተዘዋወረች የታደሰን ጉዳይ ስትጠይቅለት ዋለች፤ ፯ ሰዓት ሲሆን ታደሰ ስለ ደከሙልኝ ብድር መላሽ ያርገኝ ብሎ ሔደ።

በ፱ ሰዓት መጥቶ ተላመዳ፤ «ስለ ቀኑ ልፋትዎና ሰጣት፤ አስቴርም አመስግና ተቀበለች። ታደሰም ዝም ብሎ ሔደ። በነጋታው አር ዕለት በ፯ ሰዓት ላይ አስቴር አውቶብስ ስትጠብቅ አገኛት፤ ሰላምታ ከቤትዋ አደረሳት፤ መለማመድ በረከተ።

ቅዳሜ ዕለት ደግ አሁንም ፯ ሰዓት ላይ ወደ ቤትዋ ልትሔድ አውቶብስ ስትጠብቅ ታደሰ ደረሰና ላድርሶት ቢላት አስቴር ከጓደኝዋ ከአልማዝ ጋር አብረው ገቡ፤ መጀመሪያ ከሠራተኛ ሠፈር አልማዝን አደረሰና አስቴርን ይዟት በቀጥታ ወደ ገፈርሳ ሔደ፤ አስቴር እንኳን ቤትዋን ስታልፈው ለግዜው አልሔድም ብላ ነበር፤ ታደሰ ግን «ምናለበት? በጣም ጥሩ የሆነ አዲስ ሆቴል ቤት ተከፍቷልና ምሳ በልተን መልሶታለሁ» ብላት ገብ አለች።

አስቴር ሰው ያየኛል እያለች ብትፈራ ታደሰም ፈሪ መስሎ «ኧረ እኔም ክብሬን ማስነቀፍ ይሆንብኛል» ብሎ በሆቴል ጓሮ በር ገቡ። አንድ ሰፊ አልጋ ሰፊ ካለበት ክፍል ሆነው ምሳ አዘዙ፤ ታደሰ ሴኮንዶሚስቶ አዘዘ፤ አስቴር ደግሞ ዶሮ ጥብስ አዘዘች፤ በመጠጥ በኩልም ሁለት ቢራ አዘው በሉና ጠጡ፤ ለመብሉ ማሸራሸሪያ፤ ብሎ ውስኪ እንዲመጣላቸው አዘዘ፤ አስቴር አልጠጣም አለች፤ ታደሰ ግን ለመብሉ መድኃኒት ነው ብሎ አስመጥቶ አስጠጣት።

በልመናም በማስገደድም አስቴርንን ሁለት ብርጭቆ ውስኪ አስጠጣት፤ ሦስተኛ ተቀድቶ ተቀመጠ፤ አስቴር የተቀመጠችው ቁም ሣጥኑ አጠገብ ካለው ወንበር ላይ ነው፤ ታደሰ የተቀመጠው አልጋው ላይ ነው፤ እመሐላቸው የበሉበትና የሚጠጡበት ጠረጴዛ አለ፤ ታደሰ «ሆዴን ነፋኝ እስቲ ለወስ ልወስ ልበልበት» ብሎ ከመቀመጫው ተነሣ፤ ሁለቴ ያህል ሔድ መለስ ካለ በኋላ በድንገት የአስቴርን አንገት እቅፍ አድርጎ ያዛት፤ አስቴርም በጣም ታገለችው፤ ቧጠጠችው። አስቴር ጥፍሯ ረጃጅም ስለ ነበረ እጁን ሁሉ አደማችው ታደሰ ግን አልተሰማውም።

እንደ ምንም እየሳባት አልጋው ላይ ጣላት፤ አስቴር ከሥር ሆነች፤ ታደሰ ከላይ ሆነ አስቴር ከሥር ብትሆንም ታደሰን አንገቱን ፊቱን በጫጭራዋለች፤ ቢብስበት «ምን ላደርግሽ መስሎሽ ነው? » ቢላት «ታዲያ ልቀቀኛ» አለችው፤ «እኔ ሌላ ምንም አልፈልግም፤ ብቻ አንዴ ሳሚኝ» ቢላት «ልጮህ ነውና ትለቀኝ እንደሆነ ልቀቀኝ» አለችው፤ «የታለልሽና» ብሎ ሲታገላት ልትጮህ ስትል በከንፈሩ አፈናት፤ ለጊዜው አስቴር አፏን ወደ ግራ ወደ ቀኝ እያለች አስቸገረች፤ ታደሰ ነዶት ስለ ነከስ ቢያደርጋት ረጋች። ሳማት አስቴርም እየቆየች ላላ አለችለት፤ ጥቂት ቆይታም፤ «እባክህ ከፍነሬ እኮ ያብጥብኛል» ብትለው «እንግዲያውስ የኔ ይበጥልሽ» አላት፤ ጥቂት ቆይታም «እግሬ መሬት አልደርስ ስላለ ወገቤ እኮ ተቆረጠ» ብትለው ቀና ብሎላት እግሯን አልጋው ላይ ሰበሰበች፤ አስቴር የለበሰችው የሀገር ልብስ ስለ ነበር ነጠላዋን ጠቅላ ወንበሩ ላይ ልታስቀምጥ ስትወረውረው ጠረጴዛው ላይ ያለውን የውስኪ ብርጭቆ ስለነካው ወድቆ ተሰበረ፤ ውስኪውም ፈሰሰ፤ በዩ እንኳን ሊገባ መዝጊያውን ገፋ ቢያደርግ ስለተቆለፈበት ተመለሰ።

፲ ሰዓት ተኩል ሲሆን አስቴር ከቤትዋ ደረሰች። ለሦት ቀናት ያህል አስቴር ከታደሰ ጋር በየረፍት ጊዜዋ ከነፈች፤ ማክሰኞ ፱ ሰዓት ተኩል ገደማ ኃይለ ማርያማ ከአሰላ እቤቱ ገባ፤ ወዲያውኑ ስልክ ደውሎ መምጣቱን ለአስቴር ነገራት አላስችል ብሎትም ሊያያት ወደ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ሔደ፤ ከቢሮዋም ገብቶ አስቴርን ተገናኛት።

አስቴር ተለውጣለች፤ አስቴር አለ መጠን አጊጣለች፤ አስቱእር አኩርፋለች፤ የአስቴር ፈገግታ ከመቶው አሥሩ ነው የቀረው አስቴር በሆድዋ ነዷታል፤ ኃይለ ማርያም ሞኝ ነው፤ አልገባውም «ምን ሆንሽብኝ?.....አላት፤ «ምን ሆንኩኝ» አለችው፤ «እኔ የቆየሁት እምዬ ስላልተሻላቸው ነው፤ ተቆጣሽኝ እንዴ» አላት፤ «ሳይድኑ ምን አስቸኩሎ መጣህ? » ለመሆኑ የናት ውለታ ይሔው ነው? አይ ወንዶች፤ አፈር ይብላኝ ዋ ሴት ልጅ ብትሆን» አለችው «አሁንማ ድነዋል፤ ትናንት እንኳን እታባ ቤት ውሰደኝ ብለውኝ ወስጃቸው ሲጫወቱ ዋሉ፤ ዛሬም ድኛለሁና ሒድ ቢሉኝ ነው የመጣሁት እንዳልከርምም ልጆቼም አንቺም ናፈቃችሁ» አላት፤ «በልደህና ነው፤ አሁን ሥራዬን ልሥራ፤ ማታ እንጫወታለን» ብላው ኃይለ ማርያም አከላቱን ሊታጠብ ወደ ቤቱ ሔደ።

አስቴር ስልክ ደውላ የባሏን መምጣት ለታደሰ ነገረችው፤ ምንም መቸገር እንደማይገጥማቸው አስረዳችው፤ አስቴር ረቡዕን ሐሙስን ተመላልሳ እንደ ሠራች ታምሜአለሁና ፈቃድ ይሰጠኝ ብላ የአሥራ አምስት ቀን ፈቃድ ተቀበለች፤ ኃይለ ማርያም አያውቅም፤ ጧት በሦስት ሰዓት ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ድረስ ባሏ ኃይለ ማርያም ያደርሳታል፤ እሷም በቢሮዋ በየጓደኞችዋ ዝነት ትግባባና «ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል ልታከም መጥቼ እግረ መንገዴን ልጠይቃችሁ መጣሁ» ብላ ትወጣለች፤ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ታደሰ ጋር ተያይዘው ይሔዳሉ።

ሰባት ሰዓት ሲደርስ ማርያም አጠገብ ካለው መጠምዘዣ ላይ ባሏን ጠብቃ አብረው ይሔዳሉ፤ ኃይለ ማርያም የመጀመሪያው ዕለት «ምነው ያለወትሮሽ ከዚህ ትጠብቂኛለሽ? » ቢላት «በውስት ወደ ፓስፖርት ክፍል ተዛውሬ ስለምሠራ ከሣህሊቱ ጋር በእግሬ እዚህ ድረስ እየተጫወትሁ መጥቼ ነው፤ እስከ ፲፫ ቀንም ድረስ እዚሁ ስለምሠራ እዚሁ ጠብቀኝ»

ብላዋለች፤ በ፱ ሰዓት ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ጓሮ ካለው ፓስፖርት ክፍል ያደርሳትና ወደ ሥራው ሲሔድ ታደሰ ተቀብሏት ወደአሻቸው ይሔዳሉ።

በውነቱ ታደሰ አስቴርን ወደዳት፤ ከሷም ሌላ የሚወዳት ፈፅሞ እንደማያገኝ አወቀ፤ ስለዚህ እንዲጋቡ ጠየቃት፤ አስቴርም ጋብቻውን በደስታ ፈቀደችለት፤ ኃይለ ማርያምንም ፍታኝ አለችው፤ «ልጆቻችንስ» ቢላት «እንደፈለግህ አርጋቸው» አለችው፤ ሽማግሌዎቹም የሰጠችው መልስ ፤‹እናቱ ሳይታመሙ ታምሜአለሁና ናልኝ እያሉ ያቃጥሩታል ደግሞም አንድ ልጅ አጭተውለታልና በላዩ ሳያገባ ይፍታኝ ብቻ» የሚል ሆነ።

ብትለመንም ብትባበልም ኃይለ ማርያምም አላረኩትም ብሎ ቢምል ቢገዝትም አሻፈረኝ አለች፤ ኃይለ ማርያም ነገር ያሳመረ መስሎት «ከተጋባን ጀምሮ በ፺ ዓመታችን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ከ፪ ዓመት በፊት ቀብጪ ካንድ ሴት ዘንድ ደርሻለሁ እንጂ እንኳን ሌላ ሚስት በላይዋ ላጭና አሁን ካልኳት በስተቀር ሔጄ እንደሆነ ሰማይና መሬት ይደፋብኝ፤ የውስጥ አከላቴን ይገልብጠው» ብሎ ማለ።

አስቴር አለቀሰች፤ «እኔን ከቤት እየጎለተ እሱ ከማንም ሸርሙጣ ዘንድ መዋሉ እየመሰከረ ደሞ ታረቂ ትሉኛላችሁ፤ ብቻ እግዚአብሔር ይፍረደው፤» አለች፤ አባቷ ባላምባራስ አበበም ተናደው «ምነው ይሔ ጨምላቃ የኔ ልጅ መጫወቻህ ነች» ቢሉት ደንግጦና ነዶ ያለ ሀብታቸውን ተካፍለው ተለያዩ፤ የጉለሌው ቤት ግን በኃይለ ማርያም ደረሰው፤ ኃይለ ማርያም ለሊቱንና መሰንበቻው ሲጨነቅና እንቅልፍ አጥቶ ከረመ። በተለየም ልጆቹ «እማዬ ምነው ጠፋች? » እያሉት ስላስቸገሩት፤ ኃይለ ማርያም ሚስቱን እስቲረሳትና ልጆቿም እስቲረሷት ድረስ ትልቅ ፈተና ሲፈተን ከረመ።

//=//

አስቴር የተፋታች ዕለት ብቻ ከአባቷ ቤት አደረች፤ ከዚያ በኋላ ዓይናንም አላዩዋት፤ ከታደሰ ቤት ገባች፤ ከሥራዋም ውጪ ብሎ አስወጣት፤ አስቴር ልጆችዋን ላባታቸው አስታቅፋ እሷ የታደሰ ዘበናይ ሆነች፤ ልጆቿ አይናፍቋትም፤ ኃይለ ማርያም አይታወሳትም፤ በዚያ በግቢያቸው በአበቦቹ መሐል መስኮቶቹ ላይ በደረታቸው ጋደም ብለው

ልጆቻቸው ዙሪያውን ሲቦርቁ እነሱ ደስ የሚል ምኞት ያወጉ የነበሩበት እንኳን ትዝ አይላትም።

እሑድ ዕለት ታደሰ ለምሳው መጣና ቢቀርብለት አልበላም አለ፤ «ምነው ታዱዬ ምን ነካህ? » ብትለው «አንቺ ሸርሙጣ ባልሽን የልጆሽን አባት የከዳሽ ለኔ ትሆኝኛለሽ? አሁን ብቻ ሰው ሳይሰማ ከቤቴ ውጪ» አላት።

«እንዴት» ብትለው «እንዲሁ ነዋ» አላት፤ አስቴር ጦሙን በዋለው ሆድዋ ድብን አለችና «ከባሌ አጣልተኸኝ፤ ከሥራዬ አስወጥተኸኝ፤ ከልጆቼ ለይተኸኝ መጨረሻውን ለኔ ለትናንቱ ብለሽ ከዳሽው፤ አንቺ እኔማ ባገባሽ ብታርጅኝም አላሳዝንሽም፤ በኔስ ላይ ቢሆን ነገ እንደዚሁ ልታደርጊ አይደለም? አሁን ብቻ ሳትዋረጂ ሾለክ በይ» አላት።

«ሀብቴሳ? ይሁን በጄ ዕቃዬን ስጠኝና እሔዳለሁ» ብትለው «ወንዱን ልጅ አታለሽ ያመጣሽውን አባት ተረክቦልሻል፤ ሌላ ምን ትፈልጊያለሽ? እኔስ አልሞኝልሽምና ውጪ አባትሽን ነበር አርባ መግረፍ፤ ዘለዛላ የዘልዛላ ልጅ ዘረ ዘልዛላ አሁን ትወጪያለሽ አትወጪም? » ብሎ ከመቀመጫው ብድግ ቢልባት የሥራ ልብሷን እንደ ለበሰች ሾለክ አለች።

አስቴርን ኃይለ ማርያም ታወሳት፤ አስቱ ሲላት ጆሮዋ ላይ ተሰማት፤ ኑኑዬ የምትላት ልጅዋ አቴ ብላ ስትጠራት ሰማቻት፤ አስቴር ቦርሳዋን ይዛ ከኃይለ ማርያም ጎን ሆና ግቢውን ስትገባ ልጆቿ እየተሯሯጡ መጠው እጉያዋ ሲገቡ ታያት፤ ኃይለ ማርያም ኑኑዬን አቅፎ ኑኑይዬ እያለ ከምግብ ቤት ሲገባ በትዝታ አየችው «እባክህ ወንበሯ ላይ አስቀምጣትና ትብላ ሸሚዝህን ታቆሸሽብሃለች» ትለው ተሰማት፤ «አስቴርዬ እባሽን ደክሞኛልና እንተኛ ሲላት ሰማችው፤ «አስቴር ተኝታለችና አትንጫጩ ብሎ ሲቆጣ ሰማች፤ በትንሿ መኪናቸው እጐኑ ተቀምጣ ሽርሽር ስትሔድ አየች፤ በጫካ ውስጥ በእግራቸው ሲዘዋወሩ ቀሚሷን ጋሬጣ ሲይዝባት ሲያስለቅቅላት አየችው፤ «አስቴርዬ በግቻ ሣር ውስጥ መሔድ ባትሽን ይቧጥጠዋል፤ ነይ ከዚህ እንውጣ ሲላት ሰማችው፤ «አስቱዬ እማማ እኮ ሳምልኝ ብለውኛል፤ ልሳምሽ ሲላት «አሞኛል ያለችውን ሰማች።

አስቴር ብቻዋን እያየችና እየሰማች በቀጥታ ተጉዛ ከድሮ ቤትዋ ኃይለ ማርያማ ዘንድ ሔደች፤ አጥሩ አጠገብ ስትደርስ ልጆችዋ ሲንጫጩ

ሰማች፤ ሆድዋ ተንቦቻቦጨ፤ በግንቡ ላይ በብረቶቹ ውስጥ አሾልካ ብቃይ ኃይለ ማርያም በሰፊው መስክ መሐል ከትልቁ ጥድ ሥር አበቦቹ መሐል ድሮም አስቴርና እሱ ጋደም ብለው ይጫወቱበት ከነበረው ሥፍራ ሽሚዙን ለብሶ በደረቱ ተኝቷል፤ ጀንበሯ ለመጥለቅ የቀርበች የ፲፩ ሰዓት ደብዛዛ አንት፤ ሦስቱም ልጆቹ ሦስት ትራስ ይዘው ይደበድቡታል፤ ኃይለ ማርያም ደግሞ ዱዱ የሚለውን መሐከለኛውን ወንድ ልጁን አስተኝቶ «አንተ ደካማ አንተ ፈሪ እኔን ነው የምትደበድበው» እያለ ይኮረኩረዋል፤ ኑኑዬ ካባቷ ጀርባ ላይ ተቀምጣ በትራስ የአባቷን ራስ እየደበደበች «በልኮ ወንድሜን ልከክ» ትለዋለች፤ ትልቁ ልጁ ካሡ ደግሞ «ወንድሜን ካለከክ ዛሬ ገደል ነው ምቸምልህ» እያለ የአባቱን እግር ይስባል፤ ዱዱዬን አባቱ በደረቱ ታቅፎ ስለሚኮረኩረው ባለ ኃይሉ እየጮኸ ይስቃል፤ አስቴር ባለችበት አለቀሰች፤ ወዲያውኑ ስታይ ኃይለ ማርያም ዱዱዬን ለቆ ኑኑዬ እንዳትወድ በጁ ደግፎ ቀስ ብሎ በጀርባው ገልበጥ አለና ኑኑዬን ይዞ ያስጮሃት ጀመር ኑኑዬም « ኡ - ኡ - ፖሊስ - ፖሊስ - ና - ና - አባዬ ገደለኝ» ስትል ካሡና ዱዱ ደግሞ «ልከክኮ» እያሉ በትራስ እየደበደቡ አሳመሙት፤ ኃይለ ማርያም ዱላው ሲበረክትበት ጊዜ «መዓዛ! ኸረ አስጥይኝ ልጆቼ ገደሉኝ» ብሎ ጮኸ።

ወዲያውኑ አንድ አጠር ያእልች መልከ መልካም ሴት ቀይ ሹራብና ቢጫ ቀሚስ የለበሰች ለእድፍ መከላከያ ጌጣማ የሆነች አጠር ያለች ሰማያዊ መልክ ሐር ሽርጥ ሽብ ያደረገች ከቤት ብቅ ብላ «ልጆቼ አትተውም? » ብትላቸው ኑኑዬ ትራስዋን እንደያዘች ዞር ብላ ግንባሯን ኮስትራ ቆጣ አለችና «በኛ አባባ ምን አገባሽ? » አለቻት፤ መዓዛም መልሳ «ጠላችሁ? ብለው ሦስቱም ተሯሩጠው ሔደው ዙርያዋን አቀፏት ወዲያውኑ ልጆቹን ይዛ ገባች።

ሳያዩዋት የምታያቸው አስቴር ብሳ አለቀሰች፤ አዘነች፤ ደነገጠች፤ ለመግባትም ፈራች በቦታዋም ሌላ ስላየች ወደ ኋላዋ ምልስ አለች፤ መዓዛ የልጆቹ ሞግዚት ናት፤ ለኃይለ ማርያም ምኑም አይደለች፤ ግና ቅጥሩ ናት።

# ምዕራፍ ፮

ከበደ ደሀ ነው ከተወለደ ፳፱ ዓመቱ ነው፤ የሚኖረው ዱከም ከተባለችው ከተማ ነው፤ ዱከም ከአቃቂ በሰቃ በታች ያለች የባቡር ጣቢያ ናት፤ ከበደ በዱከም ከተማ ውስጥ የተጨበጠና የሚተማመንበት ሥራ የለውም፤ ከበደ ገንዘብ የሚገኝባቸው ከሆኑ ማንኛዎቹንም ሥራዎች ሳይሰንፍ ይሠራቸዋል። ከሀገር ቤት ለሚመጡ ሰዎች ማመልከቻም ሆነ ሌላ ነገር እየጻፈ ፶ ሣንቲም ሒሳብ ይቀበላቸዋል፤ ከበደ የአማርኛ ትምህርት የተማረው ድሬ መድኃኔ ዓለም ነው።

ከበደ አንዳንዴ ሸንኮራ በትከሻው ብርቱካን በቁና እየያዘ በመኪናም ሆነ በባቡር ለሚተላለፉ መንገደኞች ይሸጣል። በሸንብራ እሸት ወራት በእንጉብዱ ተሸክሞ ሸንኮራ እሸት በመሸጥ ሞያው የታወቀ ነው።

ከበደ አንዳንድ ጊዜ የሚመች ሥራ ሲያገኝ ነጋዴዎች በባቡርም ሆነ በመኪና እህል ሲያስጭኑ መቶ መቶ ኪሎ እየተሸከመ በመጫን ይውላል፤ በዚህም ቀን ከበደን ደስ ብሎት ይውላል፤ ከበደን ደስ የሚያሰኘው ድካሙንና ላቡን ሳያስብ ሥራው ካለቀ በኋላ አንድ ብር እስከ አንድ ብር ከሃምሳ የሚያገኛት ገንዘብ ናት።

ከበደ የርሻ ወራት በሚሆንበት ጊዜ የቀኛዝማች አባውቃውን ኮትቻ መሬት ሲያርስ እየዋለ ለውሎው ሰባ አምስት ሣንቲም ያገኛል አንዳንዴ የቀኛዝማች አባውቃው ወኪል ሲያዝንለት አንድ ብር ሞልቶ ይሰጠዋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ከበደን አይከፋው፤ «ተመስገን» ይለዋል።

ከበደ ጥሩ ሚስት አለችው፤ ከበድ ባለሞያ ሚስት አለችው፤ የከበደ ሚስት ሰነፍ የማታስገባ ናት አይከፋትም፤ አትመረርም፤ ከብደን አታበሳጨውም ከበደ ከሚያዝንባት እሷ ብታለቅስ ትወዳለች፤ የከበደ ሚስት ጥሩነሽ ትባላለች፤ ከተወለደችም፤ ፳፫ ዓመቷ ነው። ጥሩነሽ ቆንጆ ናት፤ ዘወትር የማይኳለው የጥሩነሽ ዓይን ወንዶችን በሽተኞች ያደርጋል፤ እግዚአብሔር የሚሰጠው ሳይቸግርወ ዞማውን ጠጉር ለሷ ሰጥቷታል፤ ቀለም የማይለቀለቀው ከንፈሯ ሲታይ ሌሎችን የፈጠረ እግዚአብሔር የፈጠራት አትመስልም በጠቅላላው ጥሩነሽ ስትታይ ሁለት እግዚአብሔሮች ኖረው ባፈጣጠር ተወዳድረው እሷን የፈጠረ

እግዚአብሔር ፩ኛ የሆነ ይመስላል። በሀብታሞች ቤት እንደ ጥሩነሽ ያለ ውብ «ለሞት መድኃኒት» ቢባልም አይገኝ ጥሩነሽ ውብ ናት፤ ጥሩነሽ ደሀና የደሀ ዘር ናት።

የጥሩነሽ እናት ወይዘሮ መደምደሚያ ዓይናቸውን ተተናኩሏቸው ነበርና ከዙቃላ ዱከም መጥተው በባቡርና በመኪና የሚተላለፉትን ሰዎች ገንዘብ ሲለምኑ አንድ ቀን የባቡር (የፉርጎ) መውጫ ገፍትሮ ገደላቸው፤ ያን ጊዜ ጥሩነሽን አዝለዋት ነበር፤ በታላቅ ተአምር ዳነች፤ የጥሩነሽ አባት አቶ ጭቋላ ጥሩነሽን በተወለደች በሁለት ወር ዝቋላ ተራራ ላይ እንጨት ሊሰብሩ ወጥተው የረገጡት ድንጋይ ተፈንቅሎ ገደል ገብተው ሞተዋል፤ ጥሩነሽ ወላጆችዋን የጨረሰች ገፊ ሆና አይደለም፤ ድሆችን መጨቆን የሚያውቀው እግዚአብሔ ጥሩነሽን ሥቃይ ለማሳየት አውቆ ፈጀባት።

ጥሩነሽ በተወለደች በሃያ ዓመቷ ከበደ አገባት፤ ከተጋቡም ፳ ዓመታትቸው የመጋቢት አቦ ዕለት አለፈ፤ ጥሩነሽ ለከበደ ስባት ልጆች ወልዳለታች፤ ሁለቱ ልጆችዋ ልክ የታኅሣሥ ሐና ዕለት አራት ዓመታቸው ነበር። የጥሩነሽ ሰባተኛ ልጅዋ ገና የሁለት ወር ጨቅላ ነው፤ አንድ ጊዜ ጥሩነሽ ለማና ይፍሩ የተባሉትን ልጆችዋን መንታ ስትወልድ ልትሞት ደርሳ በስንት ድካም ከበደ ለፍቶ እግዝትነ ማርያም ረድታት ወለደች።

ጥሩነሽ ቆንጆ ናት ብያችኋለሁ፤ ባለሞያም ናት ብያችኋለሁ፤ ጥሩነሽ ከከበደ ጋር ስትኖር በባቡርና በመኪና ለሚተላለፉ ሰዎች ለሊቱን ስትጋግር ያደረችውን ኅብስትና ዳቦ ቆሎ ስትሸጥ ትውላለች፤ ጀንበሯ ልትጠልቅ ዘቅዘቅ ስትልላት ደግሞ ጋግራ ያሳደረችውን እንጀራ ጉልት ወስዳ ትሸጣለች፤ ጥሩነሽ የሴት ቁንጮ ናት ማታ ማታ ከባሏና ከልጆቿ ጋር ራታቸውን ምድጃው ዳር ተቀምጠው እሳት እያነደዱ ከበሉ በኋላ የባሏን እግር ታጥባለች፤ የልጆችዋን እግር ሁሉ ትለቃልቅና መኝታቸውን አነጣጥፋ ታስተኛቸዋለች፤ አንዳንዴ እንኳ አልማዝ የምትላት ልጅዋ ልትረዳት ትሞክራለች፤ ግን አቅም የላትም።

ባሏ ከበደ ጠላ እንዳያምረው ሁል ጊዜ እየጠመቀች ከቤትዋ አታጠፋምና ከብደ ራቱን ሲበላ ይጀርምና ተኝቶ እስቲያንቀላፋው ይጠጣል፤ ጥሩነሽ ሁሉን ነገር አከናውና ልጆችዋ ሲተኙላት አንድ ፋሽኮ

ጠላ ከከበደ ራስጌ ታደርግለትና ለነገ ገበያዋ የሚሆናትን መሥራት ትጀምራለች።

መጀመሪያ ኀብስቷን ባንድ ምድጃና የገበር ምጣድ ላይ ጥዳ ያ እስቲበስል ድረስ በሌላ ምድጃ የእንጀራ ምጣድዋን ጥዳ እንጀራው እስቲበስል በምታገኘው ፋት ድስቷን ትሠራለች፤ ማታ የሠራቸው ወጥም እስተነገው ማታ ድረስ ይበቃታል።

ድስቷን ካወጣች በኋላ ያቦካችውን ሊጥ ጋግራ እስክትጨርስና ኀብስቱም (ጥቢኛ) እስቲበስል ድረስ በድስቱ ምትክ ዳቦ ቆሎ መቆራርጧን ትተካለች፤ ወዲያው በሰማው ምጣድ ዳቦ ቆሎዋን ቆላልታ ሲበስል አውጥታ ዘይትና በርበሬ አዋህዳ ካሸችው በኋላ ከድና ታኖረዋለች፤ የነገረው ገበያ ተያዘ።

ጥሩነሽ ጠቀም ያለ ትርፍ የምታገኘው ከካቲካላ ንግድ በመሆኑ በየሳምንቱ ጥዳ ውዥሞውን ተክላ በ፫ኛው ምድጃ እሳት ታነድበትና አረቄዋን ደርባ ስታወጣ ታመሻለች።

ቅዳሜ ጧት ዝነኛው የጥሩነሽ ካቲካላ ረፋድ ላይ ተሽጦ ያልቅላታል።

ጥሩነሽ የሴት ቁንጮ ናት ብያችኋላሁ፤ ጥሩነሽ የእኩልነት መብት ይገባታል፤ የምትባል ሴት ናት፤ እሷ ግን ይህን ሁሉ አታውቅም፤ ፊደል የቆጠሩ ሠለጠንን የሚሉ ሴቶቻችን በወለም ዘለም የእኩልነት መብት ይሰጠን ብለው ሲከራከሩ እንደ ጥሩነሽ ዓይነቷ ከልክስክስ ወንድ የምታስመርጠው ሴት ያ መጨቃጨቅ ባሏን ትረዳለች፤ ታስደስታለችም፤ እኔም ብሆን ኮስታራ ያለች አስደሳች ታማኝ ሚስት ባገኝ የባልነት መብቴን በሚስትነት መብቷ በለወጥኳት ነበር። የጥሩነሽ ልፋት በዛ።

ቅዳሜ ቀን ጥሩነሽ ኀብስትና ዳቦ ቆሎ ይዛ ከመኪና መንገዱ ዳር ተቀምጣለች፤ ታደሰ ከጎኑ ሥርጉተን አስቀምጦ ወደ ቢሾፍቱ (ደብረ ዘይት) ሲያልፍ ጥሩነሽን አያት፤ ጥቂት አለፍ ካለ በኋላ መኪናአውን አቆመ፤ ከብደ ሸንኮራውን አንግቦ መንደሪውን በቀለምሺሽ (ትንሽ ቁና) ይዞ ወደ መኪናው ሮጠ፤ እነ ጌታቸው እነ አወቀ ሁሉ እንደዚሁ እየያዙ ሮጡ፤ ጭቃላ እንኳ ሲሮጥ የአውራ ጎዳና መሥሪያ ቤት ላንድ ሮበር ሊድጠው እግዚአብሔር አወጣው።

በግራም በቀኝም «የኔን ግዙ ጌቶች፤ እሜትዬ ይህን የመሰለ የትም አያገኙም» እያሉ አዋከቧቸው፤ ሥርጉተ አንድ ቀለምሺሽ መንደሪን ገዝታ መኪናው ውስጥ ዘረገፈች፤ ታደሰ ግን «ዳቦ ቆሎ ነው የምፈልገው ብሎ ለፈፈ፤ ከበደ ቶሎ ብሎ «ጥሩነሽ ቶሎ በይ! » አላት፤ ጥሩነሽ ጭኗ ላይ ያጋደመችውን የ፪ ወር ልጅዋን አንስታ እስክትታቀፍ ድረስ እነ ሜልቱ እነ አበበች ዳቦቆሎአቸውን እያያዙ ሮጡ፤ ከመኪናው አጠገብ ደርሰውም «ይሕሄው ጌታዬ» ቢሉ ታደሰ ቀምሶ ሳያጣጥም «አይጣፍጥም» አላቸው።

ከበደም «አይዞሽ ቶሎ በይ ጥሩነሽ! » አላት ጥሩነሽም ባንድ እጅዋ ልጅዋን በአንድ እጅዋ ዳቦቆሎውን ይዛ የልጅዋን መታቀፊያ ጨርቅ እየጎተተች ደረሰች፤ ታደሰ የጥሩነሽን ፊት እያየ፤ «የኋላውን በር ከፍተሽ ጋዜጣው ላይ ዘርግፊ» አላት ዘረገፈች መዝጊያውን እንኳ መክፈት አጥታበት ከበደ ነው ሸንኮራውን እንደ ታቀፈ የከፈተላት።

ይሔ ሁሉ ሲሆን ታደሰ ጥሩነሽን በማየት ልቡ ተሸብሮበት ነበር፤ በኋላም ዋጋውን ሳይጠይቅ ሦስት ብር ሰጥቷት ሕሄደ፤ የጥሩነሽ ዳቦ ቆሎ ቢቸረቸር ኖሮ የሚጣራው ፶ ሣንቲም ብቻ ነበር።

ታደሰ ቅዳሜ ዕለት ሥርጉተን ይዞ ወደ ቦሾፍቱ ሲሔድ የተነጋገሩት አድረው እሑድ ማታ ወደ አዲስ አበባ እንደሚመለሱ ነው፤ ታደስና ሥርጉተ ቢሾፍቱ እንደ ደረሱ ሆቴል አረፉ፤ አንዳንድ ቢራ ጠጥተው ደከሞኝላ አንቀላፍቶኛል ተባብለው ተኙ፤ ሩብ ሰዓት ያህል እንደ ተኙ ታደሰ «የነበረብኝን ቀጠሮ ረስቼው ነውና የመጣሁት አሁን በ፱ ሰዓት አዲሳባ መድረስ አለብኝ፤ ብሎ ከመኝታቸው ተነሥተው ወደ አዲስ አበባ መልስ ሆነ። የጥሩነሽ ዳቦ ቆሎ አንዷ ስንኳ አልተበላችም ነገር ግን ተፈሳሶ ከጋዜጣው ላይ አልቋል።

ዱከም ሲደርሱ ታደሰ ዝግ ብሎ እያየ አለፈ፤ ጥሩነሽ የለችም፤ ከበደ ግን ሸንኮራውን ይዞ ቆሞ ነበርና ለጥ ብሎ እጅ ነሳው፤ «የዳቦ ቆሎዋ ሴት የት ሔደች? » ብሎ ታደሰ ቢጠይቀው «ልታሰናዳ ከቤት ሔዳለች» ሲል ከበደ መለሰለት፤ ታደሰም በሆዱ «ምነው ቅድም ባልገዛኋት ኖሮ ብሎ ምንተ እፈረቱን ለከበደ «ጥሩ ዳቦ ቆሎ ታሰናዳለች» አለውና ሥርጉተን እንደያዘ አዲሳባ ገባ።

ታደሰ ሥርጉተን ከቤትዋ አድርሶ ሲመለስ አክሎግ የተባለ ጓደኛውን ከፒያዛ አገኘው፤ በታደሰ መኪና ሁነው ሲንሸረሸሩ አክሎግ ለታደሰ ሲያወራ «ለማ ወርቅ ቤት ሔደን እንጫወት ናፍቃሃለች ቢለው ታደሰ ሲመልስለት «ጠልቻታለሁ» አለው፤ ጥቂት እንደ ቆዩ ጠቅላዩ ፖስታ ቤት በራፍ ሲደርሱ አክሎግ እንዲህ አለው «በቀደም መዓዛን አግኝቻት ምነው ጠፋችሁ? ብላ ወቀሰች፤ እስቲ አሁን እንሒድ ቢለው «ያ ልፋጭ ወንድሟ ይርጉ እያፈጠጠ ከሷ ቤት መሔዱን ጠልቼዋለሁ።

እንዳቅሙ ደግሞ እየተቆጣጠረ ሊጠብቃት ይከጅላል፤» አለ ታደሰ ሲመልስ።

አታክልት ተራ ሲደርሱ «አዜብ እኮ በጣም ትወድሃለች፤ ለምን አጠይቃትም? እስቲ አሁን እንሒድና እንዴት ነሽ እንበላት» ቢለው አክሎግ «ወይድ እባክህ ይቺን ቆፈቆፍ አሮጊት? አለው ታደሰ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት አጠገብ ሲደርሱ «እስቲ እዚህ ከደረስን ጸሐይን እንጎብኛት? » ቢለው ታደሰ ሲመልስ «እሷን ልጅ እኮ እወዳት ነበር፤ እንደት ትወደኝ ነበር መሰለህ ብቻ ያኔ ያንን መናጢ ጭባ አክሊሉን ከያዘች ወዲህ እርግፍ አርጌ ተውኳት» አለው።

ፈረሰኛው ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ደርሰው የፈረሰኛው የምኒልክን ሐውልት ሲዞሩ ሐመልማል ፫ ቁጥር አውቶብስ ስትጠብቅ ታደሰ አያትና ለአክሎግ «እያት ያቺ መናቲ ደሀ፤ ላግባሽ ብላት ተግደርድራ ያ ድሀ ባሏ በአውቶብስ ያስፏድዳታል» ቢለው «አመዳም እድሏ መች ለመኪና አላት» አለ አክሎግ ሲመልስ።

ፈረሰኛው ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ደርሰው የፈረሰኛው የምኒልክን ሐውልት ሲዞሩ ሐመልማል ፫ ቁጥር አውቶብስ ስትጠብቅ ታደሰ አያትና ለአክሎግ «እያት ያቺ መናቲ ደሀ፤ ላግባሽ ብላት ተግደርድራ ያ ድሀ ባሏ በአውቶብስ ያስፏድዳታል» ቢለው «አመዳም እድሏ መች ለመኪና አላት» አለ አክሎግ ሲመልስ።

«ይልቅስ» አለና ታደሰ «ከተማው ሰልችቶኛልና ወደ ውጪ አየር እንቀበል» ብሎ ከአግሎግ ጋር በቸርቸል ጐዳና ተዘቀዘቁ፤ ላጋር ሲደርሱ ወደ ግራ ተመዘዙ፤ መሿለኪያ ሾለኩ፤ የመኪናው ፍጠንት ፹ መታ ዮሴፍን አለፍ ሲሉ በ፸ እና በ፹ መሐል መላለስ የነበረ የፍጥነት መለኪያ

በ፺ እና በ፹ መሐል ዋለ፤ አቃቂ በሰአቃን አለፉ፤ ዱከም ደረሱ፤ የመኪናው ፍጠንት ፳ ሆነ ዘግይቶም በ፲ ረጋ።

ጥሩነሽ ዳቦ ቆሎና ጥቢኛ ይዛ ተቀምጣ ታደሰ አያት፤ ከሷ አለፍ ብሎ መኪናውን አቆመ፤ እነ አበበች ዳቦ ቆሎአቸውን እነ ጌታቸው መንደሪንና ብርቱካን እየያዙ ሮጡ፤ ካጠገቡ ደርሰው ግን ደንግጠው ተመለሱ፤ የጥሩነሽ ባል ከበደ የባቡር መግቢያ ሠዓት ስለ ነበረ የሚሸከመው ፍለጋ ስለ ሔደ በዚያ ቦታ የለም።

ሊሸጡ የመጡት እያጉረመረሙ ተመለሱ፤ አበበች እንኳን እያሽሟጠጠች፤ «ጢሩነሽ ሰውዬሽ መቶሊሻል፤ ነያ ሺጪ!» አለቻት፤ ጥሩነሽ ይሉኝታም ይሁን እፍረት ይዟት ዝም ብላ ቁጭ አለች፤ ታደሰ የመኪናውን ጥሩና ነፋ ጌታቸው ጥሩነሽ ስለ ጠራት ጥሩነሽ ባንድ እጅዋ ልጅዋን ባንድ እጅዋ ዳቦ ቆሎዋን ተሸክማ ደረሰች፤ «ተቀበለና ገልብጦ» ብሎ ታደሰ አክሎግን አዘዘው፤ ዳቦ ቆሎው ተገለበጠ።

ታደሰ ጥሩነሽ «ስንት ዓመትሽ ነው? » ቢላት «ምን ካልኩ? » አለችው።

«ከተወለድሽ

፳፫ ነው መሰለኝ

ባል አለሽ?

አዎ፤ ጋሽ ከበደ ነው፤

ወልደሻል?

አዎ

ስንት?

ሰባት

እንዴት ይሔን ሁሉ ልጅ ስትወልጂ ለምን ዝም አልሽ?

ምን ልበል?

ታደሰ አጠያየቁ ለራሱ ገርሞት ሳቅ አለና «በይ ደህና ኑሮሽ እንዴት ነው? አላት «እንደሚያዩኝ ነው» አለችው።

ባልሽን ትወጅዋለሽ?

አዎና

እንዲህ እያረገሽ ምኑን ትወጂዋለሽ፤

አዎና

እንዲህ እያደገሽ ምን ትወጂዋለሽ

እሱ ምን ያርግ እግዜር ነው፤ እሱም ይለፋል፤

እኔም እደክማለሁ አልሞላ አለን።

ገዳችን እኮ ባይስማማ ነው

እኛስ ተስማምተናል።

ምኑን ተስማማችሁ እያደኸያችሁ

ያ ሌላ ጉዳይ ነው ጌታዬ።

አትፈቺውም?

አበስኩ ገበርኩ ይበሉ ጌታዬ

እንግዲህ እናንተ ባላገሮች እኮ ችኮዎች ናችሁ፤

አይ ጌታዬ መሰደብ የለብኝም ሒሳቤን ከፍለው ልሒድ፤

ምን ሒሳብ ነው ያለኝ?

ሁለት ዶልቼና አንድ ድንቡሎ ነው።

ከዚህ ኑሮ ከተማ ሔደሽ ግርድና አትቀጠሪም?

በይ እኔ ልቅጠርሽ፤

ልጆቼ ይሞቱብኛል፤

ገንዘብ እያገኘሽ ብትረጃቸው አይሻልም፤ ይልቅ እሱማ ነው፤ ብቻ እስቲ ለሁሉም ከጋሼ ከበደ ጋር ልሞክር፤

ምን ያማክርሻል? አንቺው ቁረጪበት እንጂ፤ ደህና ነው እስቲ አስባለሁ።

ታደሰ ፈገግ ብሎ ፊቱን ወደ ቀኙ ዞሮ ለአክሎግ «አየህ እስቲ ይቺን የመሰለች ልጅ እዚህ ባላገር ጭርንቁስ ሆና ትቅር? » ቢለው አክሎግ ሲመልስ «ይቺ እንዲህ ጭቅቅታም ሆና ስትቀር ታሳዝናለች፤ አሁን ይቺን አዲሳባ ብትሔድ እንዴት በሆነች» አለ።

ታደሰ ወደ ጥሩነሽ ዞር ብሎ «በይ እንግዲህ ነገሩን ቁረጪና ነገ በዚሁ ሰዓት ጠብቂኝ» አለና አንዱን አሥር ብር ሰጣት፤ ጥሩነሽ አይታ የማታውቀውን አሥር ብር ባንዴ በማግኘቷ አእምሮዋ ዞሮ እንዳልነበረች ልትሆን ጥቂት ቀራት ታደሰም ከአክሎግ ጋር ወደ ቢሾፍቱ ወረደ።

ጥሩነሽ ደስ እንዳላት ከቤትዋ ገባች ጥሩነሽ ነገሩን አሰበችው፤ ሁሉንም አሰላሰለችው ጥሩነሽ ሁሉ ነገር መስሎ ታያት፤ ቤትዋን ጠላችው፤ ምድጃዋን ናቀችው፤ የአረቄ ማውጫ እንሥራዋ አስጠላት የዳቦ ቆሎ መሸጫ ቁናዋ አስቀየማት፤ ከከበደና ከልጆችዋ ጋር የምትተኛበት የጠፍር አልጋዋ ቀፈፋት፤ ብታየውም ቆረቆራት፤ አመድ ብቻ የሆነ ምድጃዋ መፈጠርዋን አስጠላት፤ «ወይኔ ጥሩነሽ ወይ ልጅት» ብላ ዛተች፤ መሐከለኛ ልጅዋ አልማዝ እያለቀሰች ስትሮጥ መጣችና የቆመችውን ጥሩነሽን ሁለት ጉልበቶች ታቅፋ አሻቅባ እያየች «እማዬ እምይዬ? ስሚኝ ስሚኝ እንጂ፤ ይቺ ቻልቱ መቻወቻዬን ወሰደችብኝ መልሽ በያት» ብትላት ጥሩነሽ ዓይኗን አፍዛ ከሔደችበት ዓለም መለስ ብላ «ምናባቷ ትለናለች? አመዳም የአመዳም ልጅ ገደ ቢስ መናጢ» አለችና እጅዋን መንጭቃ ጣለቻት።

ጥሩነሽ የኖረችበት ቤቷ ላንድ ቀን አዳር ስለቀፈፋት ከቤትዋ በላይ ሔዳ ከብሳናዋ ሥር ቁጭ ብላ ተከዘች፤ ዳመኖችን አልፋ አየች፤ አየሩን ሰንጥቃ ተመላከተች፤ ሰው ሳይኖር ተነጋገረች፤ ብቻዋን ሆና ብቻዋን ተጫወተች፤ « - እግዚአብሔር አሳምሮ ፈጥሮኛል - ቆንጆ ነኝ - ነኝና - ዛሬ አዲሳባ ያለች መንቃራ ሁሉ ተሽቀርቅራ ደስ ብሏት ስትኖር ምን በወጣኝ ልቆራመድ? - አላቅም - በቃ - ታዲያስ - እንዴ እኔ ምን ቸገረኝ - ነውና - ልክ ነው - ኸረ ወዲያ እቴ - ምን በወጣኝ - ሆሆይ - አዎ -

ይሁና - እኮ - ለምን ተብሎ ይቀርብኛል - እንደፈለጉ - ባክህ ወንድሜ እልፍ ካላሉ አያልፍም ተብሏል - ሆሆይ - ቢሆንስ - ለምን ተብሎ? - አቤትቴ - ጉድነው - ኤጭ - » እያለች ስትናገር ሰማኋት፤ ግማሹን በሆዷ የጻፍኩትን ጮሀ ተናገረች።

ታደሰና አክሎግ ቢሸፍቱ ወርደው ከነእታገኘሁ ጋር ሆቴል አደሩ።

//=//

ታደሰ ጥሩነሽ ከአዲስ አበባ ከቤቱ አስገባት፤ ገላዋን ተጣጥባ ጸዳች፤ አዳዲስ ልብሶች ለባብሳ አማረች፤ ጠጉርዋን ተተኩሳ ድንቀኛይቱ ውብ ሆነች፤ ሰማንያ ባይኖራትም ለታደሰ ሚስቱ ሆና ተቀመጠች፤ ታደሰ አሥራ ሁለት ቀናት ያህል ጨዋ ሆኖ በጊዜ ቤቱ ይገባ ጀመር፤ እየቆየ ማምሸት ቢጀምርና አንዳንዴ ከውጪ ቢያድር ጥሩነሽ የገባችበትን ዓለም እንጂ ታደሰ የሚፏልልበትን ዓለም አላቁረችውም አንድ ቀን ታደሰ ሰናይትን ይዞ ከቤት መጣ፤ ከጥሩነሽ ጋርም እህቴን እወቂ ብሎ አስተዋወቃት፤ ጥሩነሽም እህቱ መስላት ጠብ እርግፍ ብላ ጋበዘቻት፤ ታደሰ ወደ ሽንት ቤት ገባ አለ፤

ሰናይት ቅናትዋ ገንፍሎባት «መኪና ተፋሽ ባላገር» ብላ ጥሩነሽ ሰደበቻት፤ ጥሩነሽ ከተማ ባለማደጓ ሰባራ ብትንሆም የሰናይት ስድብ አናዷት «መንቃራ ወፍ እግር፤ የሉካንዳ ውሻ» አለቻትና የኋሊት ገርምማ አይታት ወደ ጓዳ ገባች። ወዲያውኑ ታደሰ ስለ መጣ ሰናይት እሔዳለሁ ብላ ስለተቆጣች ታደሰ ነገሩ ሳይከር ቶሎ ይዟት ወጣ።

ጥሩነሽ እያደር ይከነክናት ጀመር፤ ይቆጫታል ያንገበግባታል፤ የታደሰም ተግባር እየበዛ ስለሄደ ያስለቅሳት ጀመር። ከፋት፤ ከታደሰ ጋር ትተኛበት የነበረውን አልጋዋን በዕለት ባለ ተራዎች እየለቀቀች ከሳሎኑ ፎቴ ላይ ብቻዋን ማደርዋም አንገበገባት፤ ታደሰ ይዟቸው ከሚመጡት ጋር ሲዳራ ማየቷም አበሳጫት፤ መታዘዟም ቆጫት አንድ እቅን ብሶትዋን ሰማንያ ለሌለው ባሏ ለታደሰ ብትነግረው ከምድረ ግቢው አስወጥቶ ዘጋባት።

ጥሩነሽ የሰማንያ ባሏ ከበደ ታወሳት፤ ልጆችዋም ናፈቋት የዱከም ትዳሯ ትዝ አላት፤ ትንቀባረር የነበረት የዱከም የድህነት ጎጆዋ አባባት፤

እንዳትሔድ አፈረች፤ እንዳትቀር መጠጊያ አጣች፤ በመጨረሻው ከመንገድ ዳር ተቀምጣ ስታለቅስ ወደሬ አግኝታት ደጃው ውቤ ሰፈር ለሚያስነግዱት ለወይዘሮ ውብነሽ አሻሻጭነት ተቀጠረች።

# ምዕራፍ ፺

«........ወንድሜ......ወንድም ጋሼ.......እህት አለችኝ ብለህ ለሰዎች አታውራ......ትመካብኝ የነበረውን ያህል እፈርብኝ......ጨዋ ናት ትለኝ የነበረውን ያህል ባለጌ ናት በለኝ.....ወንድም ጋሼዬ፤ እኔን እህትን እንደሞትኩ ቁጠረኝ፤ እህቴ የናቴ ልጅ ወይኒቱ ሞተች ብለህ ከል ልበስልኝ - አንት ወንድሜ ባጠገቤ ባለመኖርህ ተጠቃሁ፤ ልበደል የማይገባኝን በደል ተበደልኩ፤ - እያለህ እንደሌለህ ተጠቅቻለሁና ከእንግዲህ ወዲያ ያለህባትንና ያለባትን ዓለም ልተዋት ነኝ - ይስፋችሁ - ወንድም ጋሼ ታደሰ ወልደ ማርያም ባንተ እውቂያ አሳቦ ክብሬን ገፈፈኝ - በጓደኞቼም ዘንዳ መዛባበቻ አደረገኝ - እህትህ የናትህ ልጅ እመካበት የነበረውን ክብሬን አብረሃም ይመጣልና እንቀበለው ብሎ ከተማሪ ቤት አውጥቶ አስገደደኝ ተሸነፍኩ - ዛሬ በማልቀስ ላይ ነኝና ከል ለብሰህ እዘንልኝ - ደሜን እያዘራሁ ታግሎ የጣለኝ ታደሰ ሲነሣ ስቆብኝ ሔደ.....» የሚሉ ቃላት ያሉበት ደብዳቤ ድሬዳዋ ላለው ለአብረሃም ደረሰው።

«ባልደርስልሽ የሞተው የእናታችን ማኅፀን ይታዘበኝ፤ ያባታችን አጥንት እሾህ ሆኖ ይውጋኝ» የሚል ቴሌ ግራም አዳሪ ተማሪ ቤት ላለችው ለወይኔቱ ደረሳት።

«......ታደሰ ብምርህ ፈጣሪ ነብሴን አይማራት - እህቴን የናቴን ልጅ አስነውረሃታልና አስነውርሃለሁ - የደበዘዘውን ልብህን ድምጥማጡን አጠፋዋለሁ - ሕይወትሕን በሕይወቴ እገዛታለሁ፤ በሕይወቴ የምገዛትን ሕይወትህን ከምድረ ገጽ አጠፋታለሁ - እህቴን እንዳስለቀስካት በድንህን አስቅበታለሁ - ወንድ ሆነህ ኖረሃል፤ ወንድ ሆኜ እመጣብሃለሁ፤ ወንድ ሆነህ ጠብቀኝ......» የሚል ቃሎች የሰፈሩበት ደብዳቤ ሐሙስ ዕለት ለታደሰ ደረሰው።

ታደሰ ለግዜው ሲያነበው ቀልድ በመሆኑ አልደነገጠም፤ እያደር ግን ከነከነው፤ ተጠራጠረ፤ ይፈራ ጀመር፤ የጻፈለትን ሰው ለማወቅ ፈለገ፤ ግና የማንኛዋ ወንድም እንደ ሆነ ለማወቅ አቃተው፤

ታደሰ ጥሩነሽ ከቤቱ ካባረረ በኋላ የሻረግ ጌጤን፤ በለጠችን፤ ወይኒቱን አገባችኋለሁ እያለ እያባበለም እያስገደደም መከበሪያ ክብራቸውን ገሶ እንዳባረራቸው ያውቃል፤ እነኝህ ሁሉ ወንድሞች እንዳሏቸውም ያውቃል።

ታደሰ እነዚህን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ሁሉ አስቧል፤ የተዋበች ወንድሞች እንኳን ትዝ ብለውት ልቅሞቃሞች መሆናቸውን አውቋል፤ ስለዚህ «አንድ ያልታወቀ የደሀ ልጅ ሲያላግጥብኝና ሊያስፈራራኝ ሲሻ ነው» የሚል ሐሳብ አደረበት፤ ነገሩንም ፈጥኖ ረሳው፤ እንዳል ነበር ሆኖ የነበረው ታደሰ እንደ ነበር ሆነ።

አብረሃም ከድሬዳዋ መጥቶ አዲስ አበባ ነው፤ ወይኒቱ እዚያው ተማሪ ቤትዋ ናት፤ አርብ ከተማሪ ቤት ወጥታ ቅዳሜና እሑድን ከወንድሟ ከአብርሃም ጋር ስትጫወት ከርማ ተመልሳለች፤ አብርሃም ታደሰ የሚጠመደብትን ዘዴና ቦታ ይፈልጋል ታደሰ በየመሸታ ቤትም ሆነ በየሴተኛ አዳሪዎች ቤት ገብረ ማርያም በሚባል ዘበኛ ከመጠበቁም ሌላ አሽከሩ ወርዶፋ ሰንጋ የማይመልሰው ጠረንገሎ ነው፤ በማንኛውም መንገድ አብርሃም አልሳከለት ብሎ እንደነደደው ደሙን እንዳፈላው ጥቂት ቀናት ከረመ።

ማክሰኞ ፫ ሰዓት ገደማ ላይ ሲሆን አንድ ቦስጠኛ ወርዶፋን አስፈርሞ አንድ ፖስታ ሰጠው፤ ታደሰ ራሴን አሞኛል ብሎ ተኝቶ አርፍዶ ነበርና የተቀበለውን ፖስታ ከመኝታ ቤት ገብቶ ለታደሰ ሰጠው።

«......ያንለት የሴትነት አእምሮዬ ገንፍሎብኝ ስላስቀየምኩህ ይቅርታ አድርግልኝ......ለመሆኑ ብቆጣህስ ጨክነህ ዝም ማለት ይገባህ ኖርዋል? እኔስ ታዘብኩህ....... ዘወትር ትመጣለህ እያልኩ በየአሩ ቀዳዳ ሳይ የለህም፤ የመኪና ጥሩንባ በሰማሁ ቁጥር እወጣለሁ፤ አላገኝህም......ምነው ጋሽ ታደሴ መጨከንህ?......አዘንኩ፤ ለመሆኑ በናፍቆትህ ስማቅቅ አታዝንልኝም?......ይህ ደብዳቤ እንደደረሰህ ናልኝና ዓይንህን እንኳን አይቼው ተመለስ.....

በፍቅርህ እጅግ የተሰቃየችው ወይኒቱ መኮንን» የሚል አነጋገር ታደሰ በደረሰው ደብዳቤ ላይ አነበበ፤ ወዲያውኑ ልብሱን ለብሶ ወደ ተማሪ ቤቱ ሔዶ ከአጥር ውጪና ግቢ ሆነው ታደሰና ወይኒቱ አወሩ፤ እጅግ አድርጋ የመውደዷን ነገር ወይኒቱ ለታደሰ ነገረችው እንባዋንም ኮለል አድርጋ አሳየችው፤ ፍቅሩ እንዳስለቀሳትም ገለጸችለት፤ ታደሰ የእተርበተበተ ተሰናብቷት ሔደ

እሑድ ራቀበት፤ ቅዳሜም ቆየበት፤ ታደሰ በተኛ ቁጥር ስለ ወይኒቱ ፍቅር ፍራሹን እየደበደበ ከንፈሩን ሲነክስ ከረመ፤ ሐሙስ ዕለት ወይኒቱ ስልክ ደውላ «ነገ ማታ እመጣለሁና ጠብቀኝ» አለችው ታደሰ ወይኒቱ በስልኩ ውስጥ ዓይቶና ስሞ አዝኖ ተሰናበታት።

አብር ዕለት ወይኒቱ ከወንድሟ ከአብርሃም ዘንድ ሔዳ ጥቂት ከተጫወተች በኋላ ወደ ታደሰ ቤት በሴይቼንቶ ሔደች፤ ታደሰ በሕልሙ እንጂ በውኑ አልመሰለው፤ አቅፎ ቢስማት ሳመችው፤ ወደ መኝታ ቤት ቢጎትታት እንቢ አለችው፤ ቢያባብላት «ሰበታ እንሒድ» አለችው ሔዱ ሰበታ ሲደርሱ ከምሽቱ ፱ ሰዓት ስለሆነ ወይኒቱ ወደ ቤታችን እንመለስ ስላለች ከመኪናዋ ሳይወርዱ በቀስታ ጉዞ ሬዲዮ እየሰሙ በጨረቃዋ ብርሃን እየተደነቁ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

ግራሮቹ ዛፎቹ ካሉበት ሜዳ ላይ ሲደርሱ ወይኒቱ «መኪናዋን አቁምና ሽንቴን ልሽና» አለችው፤ አቆመላት ወይኒቱ ከመኪናዋ ስትወርድ «አውሬ እንዳያስደነግጥሽ እንቺ ሽጉጥ ያዢ» ብሎ ሽጉጡን ሰጣ፤ ይዛ ወረደች፤ ከመኪና መንገዱ ፊት ራቅ ብላ ሔደች፤ ወዲያውኑም ጮኸች «ጋሽ ታደሰዬ አድነኝ! ተበላሁ» አለችው፤ ታደሰ ሮጦ ደረሰላት፤ ተያዘ።

በትንንቁም ጊዜ «......እቴን የናቴን ልጅ ወይኒቱን አባብለህ አስነወርካት፤ በሌሎች ስታዘብህና ስቆጭ ቤቴ መጣህባት፤ ጓዴ ሆነህ የምወዳትን ሚስቴን ቀለመወርቅን እንዳፍታኸኝ አስታውስ ባንተ ሰበብም እናት ያጣውን ልጄን በኩረ ጽዮንን አዲሳባ ቀበርኩት፤ ባንተ ሰበብ አገሩን ትቼ ድሬዳዋ ሔድኩ፤ ድርብ ግፍ ስትሠራብኝ እቴን ወይኒቱን ተጫወከባት፤ እኔ የቀለመወርቅ ባል የነበርኩት አብርሃም ነኝ፤ እኔ የወይኒቱ ታላቅ ወንድም አብርሃም ነኝ፤ ዛሬ እንገላገላለን፤ ባንተም

በመናደድ አንዘልቅም፤ ኃጢአት ሠራሁ ብዬም አልጸጸትም» የሚል ቃል ተሰማ።

በነገታው የደሰ መኪና በርዋ እንደ ተከፈተ መንገድ ዳር ቆማ መኪነኞች ሁሉ እያዩዋት አለፉ፤ ውላ አደረች፤ በእንደገናው ነጋታ መንደረተኞቹ ለዳኛ ነግረው ዳኞችና ፖሊሶች መጥተው መኪናዋን ተረከቡ፤ አባ ቶላ የተባሉ አዛውንት አሻግረው ቢመለከቱ በግራር ዛፍ ላይ ጨርቅ ሲወዛወዝ አዩ፤ ከዳኞቹ ጋርም ተሯሩጠው ቢሔዱ ታደሰ ተሰቅሎ አገኙት፤ ሽቶአል ከርፍቷል፤ ተነፋፍቷል፤ አብጧል፤ እመት ሐዋ ብቻ ለጊዜው «አፈር በሆንኩት!!» በልው ጮሁ እንጂ ሌሎቹ ምንም አልተናገሩም ሽማግሌዎቹና ፖሊሶቹ ሁኔታውን ሲያጣሉ፤ «በዚች በማትረባ ዓለም ላይ ሰዎች በሰው ልጅ ላይ ግፍ ሲሠሩ ማየትን ነፍሴ ስለተጠየፈችው መኖርን ጠልቼ ራሴን በራሴ ገድየዋለሁ፤ በኔም አሟሟት መንደረተኛውንም ሆነ ማንንም አታጉላሉ» የሚል ቃል የተጻፈበት ወረቀት በኮቱ ላይ በስፒል ተያይዛ ተገኘች።

ሸበቶው አቶ መርኔ ንባቡን ከሰሙ በኋላ «አይ የዛሬ ልጆች! ተማርን ይላሉ መንጠልጠል! አሁን እስቲ ምን አጣና ነው? ደሞ ዓለም ሰለቸችኝ ይባልልኛል! ከሰለቸችው ገዳም አይገባም» አሉ። ወይዘሮ ድንቄም «ኧረ ምንኛው ጊዜ ላይ ደረስን ባካችሁ? እንኳን መሐን የሆንኩት! ምነው ይሔን ሲያዩ ባይወለድስ እቴ? አበስኩ አበስኩ......» እያሉ አፍንቻቸውን እንደያዙ ወደ መኪናው መንገድ ሲሔዱ እንቧይ ቀሚሳቸውን ቢይዛቸው ወታደር ደምሴ አስለቀቀላቸው።


እንኮዬ አመተ ማርያም አፍንጫዋን እንደያዘች ሁለት ዘልላ እንባ አወረደችለት፤ ይህ እንኳን በዛበት ብለው እመት ይገስግሱ «ጨምላቃ ደሞ ለማነው የምታለቅሺው? » ቢሏት «ቀሬቴስ ሀጋ መላ ነዓይ ዋኒዲ ሀይቅ ዴስ? አዬ ዲኤሻ - ተነአይ ሀገዳ ሀኒዳኮ ኦኒ በኤዳይ? » አለቻቸውና አፍንጫዋን እንደያዘች ራቅ ብላ ቆመች።

አቶ ጉርሙ ጋቢያቸውን አስቀምጠ ዛፉ ላይ ወጥተው ታደሰ የተሰቀለበትን ገመድ ሲፈቱ ከሥር ሆነው አፍንጫቸውን በየቅጠሉ ወትፈው ሬሳውን ለያዙ ስዎች «ጊዜ አተሚን ኑቱዱፌ ጀረና፤ ፊኒፊሙ ማልቱ አገር ሲሴ? ፈረንጂንን ስፒን ኢሳ ሀበዱ - ኦቶ ነቢራ ዱፌ ሲላ

ገበሬ ጉዳ ሞቲ - » ብለው ሳቁናስ እውን ሁሉ አሳቁት፤ እመት አይችሉሽም መኪናው መንገድ ዳር አፍንጫቸውን በነጠላቸው አፍነው እንደ ተቀመጡ እየተነፋነፉ «ነበራ  እቴ ነበራ» አሉ።

የታደሰ ሬሳ ተመርምሮ በሞተ በ፫ኛው ቀን በዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ፤ የታደሰ ታሪክም በየጋዜጦች ላይ «በገዛ እጁ ተሰቅሎ የሞተ» በሚል አርእስት ባጭሩ ሲወራለት ከረመ።

# ስለደራሲው በጥቂቱ



ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታቸው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም 19 መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸ። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

<u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)
2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)
5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)
6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)

9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)
10. እውቀት (**ፍልስፍና**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY